
በመረዳት ረገድ ከደቀ መዛሙርቱ ይልቅ የካህናቱ አለቆች ይበልጥ ንቁ መሆናቸው ሊገርመን አይገባም:: እምነተ ድሆች ቢሆኑም፣ በዐውዳቸው መሠረት ቅዱሳት መጻሕፍትን የመተርጐም ከፍ ያለ ችሎታ ነበራቸው::

ሦስት ቀን ያህል መቃብሩን በሮማውያን ወታደሮች እንዲያስጠብቅ ጲላጦስን ለመኑት:: ጲላጦስ የሰጠው መልስ የሚያሻማ ነበር፤ «ጠባቂዎች አሏችሁ» [*echete koustodian*] ነበር ያለው:: እንዲህ ሲል፣ «ሁሉም በእጃችሁ ነው:: የፈለጋችሁትን አድርጉ» ማለቱ ነው? ወይስ፣ «የራሳችሁ የቤተ መቅደስ ጠባቂዎች አሏችሁ፤ እነርሱን እዘዙ» ማለቱ? ሁለቱም ሊሆኑ ቢችሉም፣ ቀደም ሲል ጲላጦስ ለአይሁድ ሮማውያን ጠባቂዎችን ይሰጣቸው የነበረ ይመስላል:: በመጀመሪያ፣ ለሕዝባዊ ዐመፅ መቀጣጠል ምክንያት ሊሆን የሚችል ማንኛውም ግጭት እንዳይነሣ ፈልጓል:: ሁለተኛ ከትንሣኤው በኋላ ይኸው ወሬ ለጲላጦስ እንዳይደርስ ጠባቂዎቹ ስጋት ገብቷቸው ነበር (ማቴ 28፥14):: የቤተ መቅደሱ ጠባቂዎች ግን ይህ አያሳስባቸውም:: በሌላ በኩል ደግሞ ሮማውያን ጠባቂዎች «የጠፋው» ሬሳ የአይሁድ እንደ መሆኑ መጠን መጀመሪያ ማሳወቅ የነበረባቸው ከጲላጦስ ይልቅ ለሸንጎው ነበር (ማቴ 28፥11):: ሦስተኛ፣ ጲላጦስ የመቃብሩን ደጃፍ በማኅተም አተመ:: ይህ ማለት ሸክላ ወይም ሰም ላይ የሚያርፍና ከመቃብሩ ደጃፉ ጋር የተያዘ ክር ማለት ነው:: ድንጋዩ ሲነሣ የሸክላው ወይም የሰሙ ማኅተም ይሰበራል:: እንደዚያ ማድረግ ከባድ ባይሆንም፣ ያን ማድረግ ግን ማኅተሙን ሸክላው ወይም ሰሙ ላይ ያሳረፈውን ባለ ሥልጣን መጋፋት ወይም መዳፈር ነው:: በሌላ አነጋገር የጲላጦስ ማኅተም ያረፈበትን ማኅተም መንካት የሮም መንግሥትን ሥልጣን መዳፈር ነው:: ይህ ደግሞ ቀላል የማይባል መዘዝ ያስከትላል:: ስለሆነም አነስተኛው ማኅተም ለስርቆት የመጡ ሌቦችን ያስደነግጣል:: እግዚአብሔር ግን በዚህ አይገደብም::



# ምድብ ዐሥራ ሦስት
# የኢየሱስ ትንሣኤና ዕርገት



በመጨረሻ ወደ ዋናው መልእክት መጥተናል - ወደ ትንሣኤው:: ይህ ሁኔታ በሐዋርያት ሥራም ሆነ በመልእክቶቹ ውስጥ የእምነታችን ማዕዘን ድንጋይ እንደ ሆነ ነው የታወጀው (ሐሥ 2፥22-36፤ 4፥2:33፤ 23፥6፤ 24፥15፤ ሮሜ 1፥4፤ 6፥5፤ 1ቆሮ 15፤ ኤፌ 1፥18፤ 2፥4-7፤ ፊልጵ 3፥10-11፤ 1ተሰ 4፥13-18፤ 1ጴጥ 3፥18-22፤ ራእ 20፥5-6):: እንዲያውም ጳውሎስ ከዚህም አሳብ ወደፊት እልፍ በማለት ኢየሱስ በእርግጥ ከሞት ካልተነሣ እኛ ክርስቲያኖች የምናሳዝን ፍጡሮች እንደምንሆን ይናገራል (1ቆሮ 15፥19):: ልዩነቱን የሚያመጣው ይህ ሁኔታ ነው:: ሀሳቡ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ያረጋግጣል:: እንዲህ ከሆነ ደግሞ ያለምንም ማመንታት ሙሉ በሙሉ ኢየሱስ መስቀል ላይ የፈጸመውን ሥራ ትክክለኛነት ያረጋግጣል:: እርሱ ከሞት የተነሣ ካልሆነ ግን በድፍረት ሰማዕትነትን ከተቀበለ ሰው የተለየ አይሆንም፤ እኛም ገና ከነ ኀጢአታችን ነን ማለት ነው (1ቆሮ 15፥17):: ድርጊቱ በመቃብር ላይ ድል ማግኘ ታችንንና ትንሣኤያችንን ያረጋግጣል (1ቆሮ 15፥21-22:42-44:51-54):: ሊሸነፍ ያልቻለው የሰው ልጅ ብቸኛ ጠላት አሁን ድል ሆኗል! እነዚህ ነገረ መለኮታዊ አሳቤዎች ብቻ አይደሉም:: ወንጌላውያኑ የሞትና የሕይወትን በጣም አስፈላጊ መልእክት ጽፈውልናል (እንደ ገና ሕያው መሆን!)::

ይሁን እንጂ ኢየሱስ በአካል የመነሣቱን ታሪካዊ ሐቅ የሚቀበሉት ሁሉም አይደለም:: አንዳንዶች፣ ከፍልስፍናዊ፣ ከሃይማኖታዊ ወይም፣ «ከሳይንሳዊ» ምክንያቶች የተነሣ

አይቀበሉትም:: ሆኖም፣ ወንጌሎቹ የሚቀርቡትን ታሪክ መሠረት በማድረግ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በአካል መነሣቱን የማይቀበሉ አምስት አመለካከቶች ወይም አስተሳሰቦች ከዚህ በታች ቀርበዋል::[1]

(1) የተሰረቀ አካል - ደቀ መዛሙርቱ መጥተው የኢየሱስን ሥጋ ሰረቁ፤ ከዚያም ከሞት ተነሥቶአል በማለት የፈጠራ ወሬ አስፋፉ:: ይህን አስተሳሰብ በመጀመሪያ ያቀረቡት አይሁድ ናቸው (ማቴ 28÷11-15):: ይሁን እንጂ ብዙም ሳንርቅ ሁለት ችግሮች ይገጥሙናል፤ ዓላማና ችሎታን በተመለከተ:: እነዚ ዐሥራ አንድ ፈሪ ደቀ መዛሙርት የታጠቁ የሮም ወታደሮችን በማለፍ ድንጋዩን ለማንከበለል፣ አካሉን ለመውሰድና በኋላም ከሞት ተነሥቶአል የሚል ወሬ ለማስፋፋት እንዴት ቻሉ? እንደዚያ ማድረግ ቻሉ ቢባል እንኳ ለምን? ኢየሱስን ማየቱን ሌላ ሰው ሲነግራቸው ከዐሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት አንዱ እንኳን አላመነም ነበር:: መቃብርን፣ በተለይ የተከበረን ሰው መቃብር መዳፈር ለአይሁድ እንደ ከባድ ርኩሰት ነበር:: ያም ቢሆን እንኳ፣ ተሰቅሎ እሞተ ሰው መቃብር ውስጥ ገብተው ከሬሳው ላይ የመግነዝ ጨርቁን በመግፈፍ አሳምረው ካጣጠፉ በኋላ ራቁቱን ሬሳ ይዘው የሚሄዱ አእምሮ የጐደላቸው ሌቦች ናቸው!

(2) ሰመመን ውስጥ መሆን፣ ይህ አስተሳሰብ ኢየሱስ ሰመመን ውስጥ ነበር እንጂ አልሞተም፤ በኋላ ግን ከሰመመኑ ነቃ ይላል:: ግን እስቲ ሐቆችን እናገናዝብ:: ከተገረፈ በኋላ ኢየሱስ እንዲገደል ልምድ ለነበራቸው ገዳዮች አልፎ ተሰጠና ተሰቀለ:: የአርማትያሱ ዮሴፍ የኢየሱስ ሥጋ እንዲሰጠው በጠየቀ ጊዜ፣ በእርግጥ መሞቱን እንዲያጣራ ጲላጦስ መቶ አለቃውን አዝዞ ነበር:: በዚሁ መሠረት ጐኑን በጦር በመውጋት ኢየሱስ በትክክል መሞቱን አረጋግጠዋል::

[1] በአካል የመነሣቱን ታሪካዊ እውነት በተመለከተ አሳማኝ መረጃ ለማግኘት N.L. Geisler, *The Battle for the Resurrection* ይመለከቷል (Nashville: Nelson, 1989)ን ለመመልከት ይቻላል::



ከአካሉ ደምና ውሃ መውጣቱ የሚያመለክተው ልቡ መወጋቱን ወይም መፈንዳቱን ነው:: ከዚያ በኋላ 100 ሊትር በሚመዝን ሽቱና ቅመማ ቅመም በተደረገበት የተልባ እግር ጨርቅ ተጠቀለለ:: ነፍሱ አልወጣችም ነበር ቢባል እንኳ፣ ይህ ራሱ አፍኖ ይገድለው ነበር:: ከዚያ በኋላ ቀዝቃዛ መቃብር ውስጥ እንዲገባ ተደርጐ የመቃብሩ ደጃፍ በትልቅ ድንጋይ ተዘጋ:: እንዲህ ያለውን አካላዊ ጉዳት ተቋቁሞ በኋላም ከመቃብር አምልጦ መሄድ፣ ከትንሣኤው ያላነሰ ተአምር ነው::

(3) የተሣሣተ መቃብር፣ በመጀመሪያ ሴቶቹ፣ በኋላም ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ ተሳሳተ መቃብር ሄደው ሲያጡት ኢየሱስ ተነሥቷል ብለው አሰቡ:: ይሁን እንጂ የመቃብሩ ሥፍራ የግለ ሰብ እንጂ የሕዝብ አልነበረም:: ሊያሳስት የሚችል ሌላ መቃብር በአቅራቢያው አልነበረም:: ከዚያም በላይ ሌላው ቢቀር የኢየሱስ እናት ማርያም የልጇ ሥጋ ያረፈበትን በተለይ በትልቅ ድንጋይ የተዘጋውንና በወታደሮች የሚጠበቀውን መቃብር በዚህ አጭር ጊዜ ይጠፋታል ብሎ ማሰብ አዳጋች ነው:: የዚህ አስተሳሰብ ትልቁ ችግር የኢየሱስ ሥጋ የት እንደ ነበርና፣ የሸንጐ አባላቱ በበዓለ ሃምሳ ዕለት አውጥተው ለሕዝብ ያላሳዩት ለምን እንደ ነበር መግለጽ አለመቻሉ ነው::

(4) የቁም ቅዠት፣ ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ከሞት እንደሚነሣ በጉጉት ይጠብቁ ስለ ነበር፣ ይኸው ጉጉታቸው ያመጣባቸው የቁም ቅዠት እርሱን ያዩ እንዲመስላቸው አደረገ:: ሥነ ልቦናዊ ጥናት ግን ይህ በፍጹም ሊሆን የማይችል መሆኑን በሚገባ አሳይቷል:: የተወሰኑ ሰዎች ያሉበት ቡድን ሁሉም በአንድ ጊዜ አንድ ዓይነት የቁም ቅዠት አይኖራቸውም (1ቆሮ 15÷6 ጋር ያነ):: የቁም ቅዠት የሚኖራቸው አንድ ዓይነት የአእምሮ መቃወስ ያለባቸው ሰዎች ናቸው:: ምናልባትም ሁለቱ ወይም ሦስቱ በሕይወታቸው አንድ ደረጃ ላይ እንዲህ ያለ መቃወስ ገጥሟቸው ነበር ለማለት ይቻላል፤ ሁሉም

በአንድ ጊዜ በቁማቸው ቃገፍ ማለት ግን አይቻልም። በጣም የባሰው ደግሞ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ እንኳ ኢየሱስ ይነሣል ብለው ጠብቀው ያልነበረ መሆኑና በዚህ ምክንያት በቁም ቃገፍ ማለት አለመቻሉ ነው። ይህኛው አስተሳሰብም ቢሆን የኢየሱስን ሥጋ በተመለከተ በቂ ገለጻ ለማቅረብ አልቻለም።

ከዚሁ ጋር የሚያያዘው ሌላ አስተሳሰብ የኢየሱስ ትንሣኤ መንፈሳዊ እንጂ አካላዊ አልነበረም የሚለው ነው። ስለሆነም ደቀ መዛሙርቱ ያዩት፣ «ክርስቶሳዊ መገለጥን» (ራእይ መሰል ነገር) እንጂ፣ በእርግጥ የኢየሱስን አካል አልነበረም። ወንጌሎቹ የሚናገሩት ይህን አይደለም። የእነርሱ ፍላጐት ኢየሱስ በአካል መነሣቱን እንድናምን ነው። ስለሆነም በአካል መነሣቱን የማይቀበል ማንኛውም አስተሳሰብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ[2] ወይም ፍልስፍናዊ[3] ድጋፍ አይኖረውም።

(5) ተራ ተረት ነው፣ ወንጌሎቹ ጥቂት ታሪካዊ እውነት ያላቸው ልብ ወለድ ጽሑፎች ናቸው። ይሁን እንጂ ሥነ ጽሑፋዊ ፈጠራ ቢሆን ኖሮ፣ አሁን ካሉን የተለዩ ወንጌሎች ይኖሩን ነበር።[4]

[2] N.L. Geisler, "The Significance of Christ's Physical Resurrection," *BibSac* 146 (1989): 148-170.

[3] S.T. Davis, "Was Jesus Raised Bodily?" *CSR* 14/2 (1985): 140-152 and G.J. Hughes, "Dead Theories, Live Metaphors and Resurrection," *HeyJ* 29 (1988): 313-328.

[4] ከነበሩበት የአይሁድና ሔለናውያን ባሕል አንጻር የወንጌሎቹ ጸሐፊዎች ትንሣኤውን በተመለከተ የፈጠራ ጽሑፍ ለማቅረብ እንደማይችሉ ሩስ ደድሪ የተባለው ጸሐፊ ያመለክታል። ለምሳሌ፣ ሔለናውያን አካል በሞት ጥላ ውስጥ ይሆናል፤ ይህም ሁኔታ በትንሣኤ ጊዜ አካሉን አይይዘውም ይላሉ፤ ሔለናውያን በሞት ጊዜ ስለ ትንሣኤው የተነገሩ ታሪኮች የፈጠራ ተረቶች እንጂ ታሪካዊ ሐቅ ባይሆኑ ኖሮ ግሪክና ሮም ውስጥ ፈላስፎች ሊገጥማቸው የሚችለውን ሙግት አለማሰባቸው የአስተሳሰባቸውን ደካማነት ያመለክታል። Ross Dudrey, "What the Writers Should Have Done Better: A Case for the Resurrection of Jesus Based on Ancient Criticisms of Resurrection Reports," *SCJ* 3 (Spring, 2000): 35-54. ከዚህም በላይ ፒ.ቦልት



ለምሳሌ የመጀመሪያዎቹ ምስክሮች ሴቶች አይሆኑም ነበር።[5] ጴጥሮስና ባልጀሮቹ ሲጠብቁት እንደ ነበርና ወዲውኑ እንዳመኑ ተደርጐ ይቀርብ ነበር። ከሞት ሲነሣ አየሁ የሚል ሰው ምስክርነት ይቀርብ ነበር።[6] ዋናው መሠረታዊ ነገር «በኋላ ከተጻፉ አዋልድ መጻሕፍት ጋር ሲነጻጸር (ለምሳሌ የጴጥሮስ ወንጌል 9፥35-11፥44 የመሳሰሉ) ወንጌላውያኑ የጻፉት ቁጥብነትና ልዝብነት ባለበት ሁኔታ መሆኑ ነው» (Carson, p. 588)። የምናነበው ሥነ ጽሑፋዊ ፈጠራ ሳይሆን ታሪካዊ ሐቅና ደቀ መዛሙርቱ ያመኑበትን ጉዳይ ነው።[7]

ትንሣኤውን የሚደግፉ ማስረጃዎች እጅግ አሳማኝ ናቸው። የጌታን በአካል መነሣት የሚያመለክቱ የተወሰኑ ማስረጃዎች አሉ፤ (1)

የተባለው ሰው ከጀግና አፈ ታሪኮች ወይም ጭብጡን ከመተርጐም ጋር የተያያዙ ፈጠራዎችን የሚደግፉ ወገኖች ነጥቡን ይስታሉ ብሏል። "Mark 16:1-8: The Empty Tomb of a Hero," *TB* 47/1 (1996): 27-38.

[5] በአይሁድ ባሕል ሴቶች እንደ ሕጋዊ ምስክር ስለማይቈጠሩ በዋነኛነት እነርሱን ምስክር ማድረግ በጣም ያልተለመደ ነበር። ጆሴፈስ (ዮሴፍ ወልደ ኮሪዮን) እንዲህ ይላል፣ «ከንዝህላልነታቸው ወይም ጾታቸው ካሳደረባቸው አጉል ድፍረት የተነሣ የሴቶች ምስክርነት ተቀባይነት አይኑረው» (*Ant* 4.219)። ይሁን እንጂ ጂ.ኦ. ኪሊንስ እና ዲ. ኬንዶል እንደሚያመለክቱት በተለይ ማርያም መግደላዊት ዋና የኢየሱስ ትንሣኤ ምስክር ናት። ስለ ትንሣኤ ከሚመለከቱ ስድስት ገለጻዎች (ማር 16፥1-8:9-20፤ ማቴ 28፥1-20፤ ሉቃ 23፥56፤ 24፥53፤ ዮሐ 20፥1-29፤ 21፥1-23) ውስጥ በአምስቱ ማርያም መግደላዊት (ሁሌም መጀመሪያ በመሆን) ተጠቅሳለች። በእርግጥ ይህ የመጀመሪያው መቶኛ ዓመት ፈጠራ አይደለም (cf. G. O' Collins & D. Kendall, "Mary Magdalene as Major Witness to Jesus' Resurrection," *TS* 48 [1987]: 631-646).

[6] ሌሎች ተጨማሪ ጽሑፎች ቢኖሩ ኖሮ ኢየሱስ ወደ ሲኦል መውረዱን ከሚያረጋግጡ ትንቢቶች ለመጥቀስ ይቻል ነበር፤ ስለ ኢየሱስ ትንሣኤ አካልና፣ ለማያምኑ የሸንጐ አባሎች ስለ ተገለጸበት ሁኔታም ይነገር ነበር።

[7] የW.L.Craig. "The Historicity of the Empty Tomb of Jesus," *NTS* 31 (1985): 39-67 ወንጌላውያኑ ትንሣኤው ታሪካዊ ሐቅ መሆኑን ያቀረቡበትን ሁኔታ ያሳያል። በጣም ደስ የሚለው ደግሞ የተጠራጣሪዎች ትችት በዚህ ዘመን ምሁራን አካባቢ አለመሰማቱ ነው። ባዶው መቃብር ታሪካዊ ሐቅ መሆኑ በስፋት ተቀባይነት እያገኘ መጥቷል። እንዲያውም የቀደሙ ጸረ ክርስትና ተቺዎች በኢየሱስ ትንሣኤ እውነተኛነት ላይ ያቀርቡት ለነበረው ተቃውሞ እንደ መሠረት ሆኗል።

ኢየሱስ ከሞተ ጥቂት ቀኖች በኋላ፣ በሞተበት ቦታ አቅራቢያ በበዓለ ሃምሳ ዕለት ከ3000 በላይ ሰዎች በእርሱ ማመናቸው፣ (2) የጴጥሮስና የጳውሎስ መለወጥ፣ (3) የሐዋርያቱ የሰማዕትነት ሞት፣ (4) የጥምቀትና የጌታ ራት ሥርዓት ዘወትር ሲፈጽሙ መኖራቸው፣ (5) የአምልኮ ቀን ከሰንበት (ቅዳሜ) ወደ እሑድ (ለምሳሌ ሐሥ 20÷7) መለወጡ፣ (6) ይህ በእርግጥ የተፈጸመ ጉዳይ መሆኑን የጥንት ቤተ ክርስቲያን የማያወላውል ምስክርነት፣ (7) በታሪክ ውስጥ በሚሊዮኖች የሚቈጠሩ ክርስቲያኖች ሕይወት መለወጥ::[8]

ከዚህም በተጨማሪ ስለ ትንሣኤ በሚናገሩ የወንጌል ምንባቦች መካከል የሐሳብ መለያየት እንዳይኖር ይደረግ ነበር::[9] ምናልባት እንዲህ ሊሆን የቻለው ሁኔታው አስገራሚ በመሆኑ፣ ታሪኩን አሳጥሮ ለማቅረብ በመፈለጉ፣ ኢየሱስን ሲያዩ የነበራቸውን ሁኔታ በየግላቸው በማቅረባቸው ወይም እያንዳንዱ ወንጌላዊ ጽሑፉን ሲደመድም አጽንዖት መስጠት ከፈለገው ነገረ መለኮታዊ ፋይዳ አንጻር ሊሆን ይችላል:: ምንም እንኳ ያሉት የሐሳብ መለያቶች ህብር የሚጎድላቸው ቢሆኑ መታረቅ የማይችሉ ቅራኔዎች ናቸው ወይም ታሪካዊ ሐቀኝነት የላቸውም ማለት አይደለም:: ስለዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ቢገጥመን እንኳ የወንጌልን ማዕከላዊ እውነት ማለት ኢየሱስ ሕያው መሆኑን! መጠራጠር አይኖርብንም::

---

[8] N.T. Wright, In *Jesus the Victory of God* (Minneapolis: Fortress (1996) ገጽ 10 ላይ፣ «መሪያቸው ከሞተ በኋላ በማንኛውም መልኩ ቢሆን እንደ ገና ሕያው ሆኗል ስለሚሉ ወገኖች አንዱ እንኳ አልሰማንም» ይላል:: የአይሁድ ታላላቅ ሰዎች ከሞቱ በኋላ ከሞላ ጐደል እንቅስቃሴያቸውም ይሞታል:: ይህ እውነት መሆኑ በመጥምቁ ዮሐንስ፣ በገሊላው ይሁዳ፣ በስምዖን አትሮንጌስ፣ በኤሊዔዘር ቤን ዲይናየስ፣ እስክንድር፣ ሜናሐም፣ ስምዖን ባር ግሌራና ባር ኮቺባ ታይቷል:: በተጨማሪ P. Bolt, "Empty Tomb of a Hero," 27-37 ይመለከቷል::

[9] C.E.B. Cranfield, "The Resurrection of Jesus Christ," *ExpT* 101 (1990): 167-172 የትንሣኤውን ታሪክ በተመለከተ የሚቃረኑ የሚመስሉ 10 ነጥቦችን ካቀረበ በኋላ ለእያንዳንዱ ምክንያታዊ ገለጻዎች አቅርቧል::



**§ 169-171**
**ሴቶቹ መቃብሩ ባዶ ሆኖ አገኙ (ማቴ 28÷1-8፤ ማር 16÷1-8፤ ሉቃ 24÷1-9፤ ዮሐ 20÷1)**

[ማር 16]1ሰንበት ካለፈ በኋላ መግደላዊት ማርያም፣ የያዕቆብ [ዮናትቃ] እናት ማርያምና ሰሎሜ ሄደው የኢየሱስን ሥጋ ለመቀባት ሽቱ ገዙ::

[ማቴ 28]1ሰንበት ካለፈ በኋላ፣ በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን ጐህ ሲቀድ፣ ማርያም መግደላዊትና ሌላዋ ማርያም መቃብሩን ሊያዩ ሄዱ::

[2]በድንገት ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፤ የጌታም መልአክ ከሰማይ ወርዶ ወደ መቃብሩ በመሄድ ድንጋዩን አንከባሎ በላዩ ላይ ተቀመጠበት፤ [3]መልኩ እንደ መብረቅ ብሩህ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበር:: [4]ጠባቂዎቹ መልአኩን ከመፍራት የተነሣ ተንቀጠቀጡ፤ እንደ በድንም ሆኑ::

ዐርብ ከሰዓት በኋላ (ሉቃ 23÷56) እና ቅዳሜ ምሽት (ማር 16÷1) ላይ እነዚያ ሴቶች ለኢየሱስ ሥጋ የሚያስፈልጋቸውን ሽቱና ቅመማ ቅመም ለመግዛት ወዲያ ወዲህ ይሉ ነበር:: እሑድ ጠዋት ከፈራረሰው በድን የሚወጣውን ጠረን ማስወገድ አይቻልም፤ ቀደም ሲል ኒቆዲሞስ 100 ሊትር የሚመዝን ሽቱና ቅመማ ቅመም ስላደረገበት ሌላ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል (?):: ይሁን እንጂ የሞተውን ሰው ሽቱ መቀባት ፍቅርና አክብሮትን ያመለክታል፤ እነዚህ ሴቶች በዚህ የሚታሙ አይደሉም:: ቀጥሎ ያለው ሰንጠረዥ ከሴቶቹ እነማን መቃብሩ ቦታ እንደ ተገኙ እያንዳንዱ ወንጌላዊ የሚናገረውን ያሳያል:: ምናልባት ሁሉም ወደ መቃብሩ ሄደው ነበር ለማለት ቢቻልም፣ የግድ እንደዚያ ነው ማለት አይደለም::[10]

---

[10] J. Wenham, *Easter Enigma* (Grand Rapids: Baker, 1984), ገጽ 82-84 ከዮሐንስ ቤት በመነሣት ማርያም መግደላዊት፣ የቀልዮጳ ሚስት ማርያምና ሰሎሜ አብረው ወደ መቃብሩ እንደ ሄዱ ያመለክታል:: ዮሐና እና፣ «ሶሰና» ደግሞ ከሐስሞኒያን ቤተ መንግሥት ተነሥተው አብረው ሄዱ::

| ማቴ 28÷1 | ማርቆስ 16÷1 | ሉቃ 24÷10 | ዮሐ 20÷1-2 |
|---|---|---|---|
| ማርያም መግደላዊት | ማርያም መግደላዊት | ማያርም መግደላዊት | ማርያም መግደላዊት |
| ማርያም የያዕቆብ እናት | ማርያም የያዕቆብ እናት | ማርያም የያዕቆብ እናት | |
| | ሰሎሜ | | |
| | | ዮሐና | |
| | | ሎሎች | «እኛ» (ቁ· 2) |

ገና ጭለማ ሳለ ወደ መቃብሩ ሄዱ (ዮሐ 20÷1):: መንገድ ላይ ሳሉ ፀሐይ በስተ ምሥራቅ በነበረው የደብረ ዘይት ተራራ አናት ብቅ በማለት ላይ ነበረች:: ድንገት ከባድ የምድር መናወጥ ሆነ:: ቀድሞውኑ ፈርተው የነበሩት ሴቶች ይብስ ደነገጡ:: ቢሆንም የጠባቂዎቹን ያህል አልፈሩም:: እነዚህ ሰዎች ምን እንዳዩ አናውቅም:: «የሆነውን ሁሉ» ለካህናት አለቆች አወሩላቸው በማለት የሚነግረን ማቴዎስ ብቻ ነው (ማቴ 28÷11):: በማቴዎስ 28÷3-4 መሠረት አንጸባራቂው መልአክ ከሰማይ ሲወርድ፣ ድንጋዩን በቀላሉ ሲያንከባልለውና በላዩ ሲቀመጥ አይተው ይሆናል:: ለሸንጐ አባሎቹ የተናገሩትን መሠረት በማድረግ፣ እነርሱ ራሳቸው መቃብሩ ባዶ መሆኑን አረጋግጠዋል:: ትንሣኤውን በተመለከተ የዓይን ምስክር ለመሆን የሚችሉት እነዚህ ጠባቂዎች ብቻ ናቸው:: ኢየሱስ ከመቃብር የወጣው መልአኩ ድንጋዩን ባንከባለለ ጊዜ ቢሆን ኖሮ፣ ጠባቂዎቹ ምንም ለማየት አይችሉም ነበር:: ድንጋዩ በቦታው እያለም ኢየሱስ ከመቃብሩ ለመውጣት ይችል ነበር (ዮሐ 20÷26 ጋር ያነ)::



[2]በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን ጠዋት በማለዳ፣
ገና ፀሐይ እንደ ወጣች (ገና ጨለማ ሳለ[ዮሐ]) ወደ
መቃብሩ በመሄድ ላይ ሳሉ፣ [3]«ድንጋዩን ከመቃብሩ
ደጃፍ ላይ ማን ያንከባልልናል» በማለት እርስ በርሳቸው
ይነጋገሩ ነበር::

ማር 16÷2-4 ዮሐ 20÷1 ጋር

[4]ቀና ብለው ሲመለከቱ፣ በጣም ትልቅ የነበረው ድንጋይ ከደጃፉ ላይ ተንከባሎ አዩ::

[3]ወደ ውስጥ ዘልቀው በገቡ ጊዜ ግን የጌታ
ኢየሱስን ሥጋ አላገኙም:: [4]በሁኔታው ግራ ተጋብተው
ሳሉ፣ እነሆ እጅግ የሚያንጸባርቅ ልብስ የለበሱ ሁለት
ሰዎች (ጐልማሳ[ማር]) ድንገት አጠገባቸው ቆሙ (በቀኝ
በኩል ተቀምጦ[ማር])::

ሉቃ 24÷3-4 ማር 16÷5 ጋር

የምድር መናወጡ ሲያበቃ እነዚያ ምስኪን ሴቶች ወደ እውነታው ተመለሱ:: «የኢየሱስን ሥጋ ሽቱ እንድንቀባው ያን ትልቅ ድንጋይ ማን ያንከባልልናል?» ይባባሉ ጀመር:: እንዲህ እየተባባሉ መቃብሩ ወዳለበት ሲደርሱ ድንጋዩ ተንከባሎ አገኙት:: ያ እንዴት እንደ ሆነ ገና አላወቁም ነበር::

ወደ መቃብሩ ሲገቡ፣ ከድንጋዩ መንከባለል ይበልጥ የሚገርም ሌላ ነገር ገጠማቸው:: ሥጋው በቦታው አልነበረም! ማን ወሰደው? የት አኖሩት?! የራሳቸውን መላ ምት ከመደርደራቸው በፊት ሌላ እጅግ የሚገርም ነገር አዩ:: መቃብሩ ውስጥ እንደ መብረቅ የሚያበራ ነጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች ቆመው ነበር::[11] እነርሱ ራሳቸው

[11] ማቴዎስ በግልጽ መላእክት በስፍራው እንደ ነበሩ ይናገራል:: ማርቆስና ሉቃስ መላእክት መሆናቸውን ያወቁት በልብሳቸው ነበር (ሉቃ 24÷23 ጋር ያነ):: በተጨማሪም ማቴዎስና ማርቆስ ትኩረታቸውን ያደረጉት ይናገር በነበረው መልአክ ላይ ሲሆን፣ ሉቃስ ግን ስለ ሁለት ሰዎች ሰፋ ያለ ገለጻ አቅርቧል (ዮሐ 20÷12 ጋር ያነ):: ይህ አዲስ ነገር አይደለም (ማቴ 8÷28፤

ሳያውቁት፣ በጉልበታቸው ተንበርክከው በግንባራቸው መሬት ላይ ተደፉ::

ሉቃ 24÷5-8
ማቴ 28÷5-6፤
ማር 16÷6 ጋር

[5]ሴቶቹም ከመፍራታቸው የነተሣ ወደ ምድር አቀርቅረው ሳሉ፣ ሰዎቹ (መልአኩ[ማቴ]) እንዲህ አሏቸው፤ (አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንደምትፈልጉ አውቃለሁና[ማቴ]) (የናዝሬቱን ኢየሱስን ነው[ማር]) «ሕያው
የሆነውን እርሱን ለምን ከሙታን መካከል ትፈልጋላችሁ? [6]እርሱ ተነሥቶአል! እዚህ የለም፤ (ኑና ተኝቶበት የነበረውን ቦታ እዩ[ማቴ]) ደግሞም በገሊላ በነበረ ጊዜ ምን እንዳላችሁ አስታውሱ፤ [7]የሰው ልጅ በኀጢአተኞች እጅ ሲሰጥ፣ ሊሰቀልና በሦስተኛ
ው ቀን ሊነሣ ይገባል ብሉ ነበርና:: [8]ሴቶቹም በዚህ ጊዜ ቃሉን አስታወሱ::

ማቴ 28÷7፤
ማር 16÷7 ጋር

[7]አሁንም ፈጥናችሁ ሂዱና ለደቀ መዛሙርቱ፣ (እና ለጴጥሮስ[ማር]) ከሙታን ተነሥቶአል፤ ቀድሞአችሁ ወደ ገሊላ ይሄዳል፤ በዚያ ታዩታላችሁ ብላችሁ ንገሯቸው:: እንግዲህ ነግሬአችኋለሁ!»

መልአኩ፣ «አትፍሩ» በማለት አበረታታቸው:: በመጀመሪያ የተናገረው ይህን ነበር (ማቴ 1÷20፤ 28÷5:10፤ ሉቃ 1÷13:30፤ 2÷10፤ ሐሥ 18÷9፤ 27÷24):: ግልጹን ነበር የተናገረው:: ከሰማያዊ ዕይታ አንጻር ይህ በጣም ግልጽ ነው:: ኢየሱስ ስለ ትንሣኤው ደጋግሞ ተናግሮአል (ማቴ 16÷21፤ 17÷23፤ 20÷19፤ ሉቃ 9÷22:43-45፤ 18÷31-33):: ያደረገው የተናገረውንና ለመለኮታዊ ባሕርዩ የሚገባውን ነበር:: ለማመን ለምን ይከብዳል? መልአኩ በሴቶቹ አለማመን የተገረመ ይመስላል:: መልአኩ የሆነውን ሁሉ በፍጥነት

20÷30 እና ተጓዳኞቹ ጋር ያነ):: ሉቃስ ትኩረት የሰጠው የሁለት ሰዎች ምስክርነት ሕጋዊ በመሆኑ ላይ ነው::



ለሰዎቹ (በተለይም ለጴጥሮስ) እንዲነግሩ አዘዛቸው:: ኢየሱስን በገሊላ ሊያገኙት ነው:: ሁሉም የተጀመረው በገሊላ እንደ መሆኑ መጠን ይህ መደረጉ ተገቢ ነው:: የአሕዛብ አገልግሎቱን ከዚያ መጀመሩም ተገቢ ነበር:: እንዲህ ማለት ግን ኢየሱስ ኢየሩሳሌም ውስጥ አይታያቸውም ማለት አይደለም:: እንዲያውም በቀጣዩ ሳምንት የፋሲካ በዓል በሚከበርበት ጊዜ በተደጋጋሚ ይገለጥላቸዋል:: ከፋሲካ በኋላ መኖሪያቸው ወደ ሆነው ገሊላ ተመልሰው ከጌታ ተጨማሪ መመሪያ እስኪያገኙ ድረስ መቆየት ይኖርባቸዋል:: ከአንድ ወር በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው በዓለ ሃምሳን ያከብራሉ:: እንደ ደንቡ የመንጻት ሥርዓትን ለመፈጸም እዚያ መድረስ ያለባቸው ቀደም ብለውነው:: ኢየሱስ ከደብረ ዘይት ተራራ ወደ ሰማይ የሚያርገው በዚህ ጊዜ ማለት ከበዓለ ሃምሳ ዐሥር ቀን በፊት ይሆናል::[12]

ማር 16÷8
ማቴ 28÷8 ጋር

[8]ሴቶቹም እየተንቀጠቀጡና እየተደነቁ (በደስታ ተሞልተው[ማቴ]) ከመቃብሩ ሸሽተው ወጡ፤ ፈርተው ስለ ነበር ለማንም አንዳች አልተናገሩም::

ሉቃ 24÷9፤

[9]ሴቶቹ ከመቃብሩ ስፍራ ተመልሰው ይህን ሁሉ ነገር ለዐሥራ አንዱና ለተቀሩት ሁሉ ነገሯቸው::

ሴቶቹ ፈርተዋል፤ ግራ ተጋብተዋል፤ በደስታ ፈንድቀዋል:: ለዐሥራ አንዱ ለመናገር ቸኩለው ስለ ነበር መንገድ ላይ ከሚያገኙት

[12] እጥር ምጥን ያለው የሉቃስ ታሪክ ኢየሱስ በኢየሩሳሌም መታየቱን ብቻ ነው የሚነግረን:: በሌላ በኩል ደግሞ፣ በገሊላ መታየቱን ያጠነክራል:: ሲ.ኤፍ.ዲ. ሞል የተባለው ጸሐፊ እንደሚያመለክተው፣ ሰዎች ከኢየሩሳሌም ወደ ገሊላ መመለሳቸው የተለመደ ከመሆኑ አንጻር ይህ ቅራኔ ሊሆን አይችልም ("The Post-Resurrection Appearances in the Light of Festival Pilgrimages," *NTS* 4 [1957-58]: 58-61).

ማንኛውም ሰው ጋር ሳይነጋገሩ በፍጥነት ሮጡ፡፡[13] እንደሚጠበቀው ሪፖርታቸው ጴጥሮስና ዮሐንስ ላይ ያነጣጠረ ነበር፡፡ ዘጠኙ ደቀ መዛሙርት አንድ ቦታ ተሸሽገዋል፡፡ ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ማመን እየከበዳቸው ነገሩን ከአካባቢው ይሰሙ ነበር፡፡

### § 172 ጴጥሮስና ዮሐንስ ባዶውን መቃብር አዩ (ሉቃ 24፥9-12፤ ዮሐ 20፥2-10)

[ዮሐ 20]2ስለዚህም (ማርያም መግደላዊት፣ ከዮና ማርያም የያዕቆብ እናትና ከሌሎችም ጋር[ሉቃ]) ወደ ስምዖን ጴጥሮስና ኢየሱስ ይወደው ወደ ነበረው ሌላው ደቀ መዝሙር (ወደ ዐሥራ አንዱና ወደ ሌሎች ሁሉ[ሉቃ]) እየሮጠች መጥታ፣ «ጌታን ከመቃብር አውጥተው ወስደውታል፤ የት እንዳኖሩትም አናውቅም» አለቻቸው፡፡ (እነርሱ ግን ሴቶቹ የተናገሩት ቃል መቀባዠር ስለ መሰላቸው አላመኗቸውም[ሉቃ])፡፡

እዚህ ላይ በሉቃስና በዮሐንስ አቀራረብ አለመጣጣም ያለ ይመስላል፡፡ ዮሐንስ ያተኮረው በማርያምና በእርሷ አለማመን ላይ ነበር፡፡ የኢየሱስ ሥጋ ተሰርቆ መወሰዱን እንጂ መላእክቱ (ሉቃስ

[13] ማርቆስ 16፥8 ማርቆስ ራሱ የጻፈው የመጨረሻ ቃል ሊሆን ይችላል፡፡ ከቍጥር 9-20 በማርቆስ አጻጻፍ የቃላት አጠቃቀም አልተጻፉም፤ የጸሐፊውን ማንነት በተመለከተ ችግር ያለባቸው ናቸው፡፡ ግን፣ ማርቆስ ወንጌሉን የደመደመው ቍጥር 8 ላይ ነው ለማለት ይቻላል? እንደዚያ ከሆነ፣ ማርቆስ ወንጌሉን ያበቃው ከሞት ተነሥቶ በአካል በታየው ኢየሱስ ታሪክ ሳይሆን፣ በፍርሃት ነበር ማለት ነው፤ በግሪክኛው መሠረት የመጽሐፉ መጨረሻ ቃል ያበቃው *gar* በሚለው መስተጻምር ሲሆን፣ «ስለ» ወይም፣ «ምክንያቱም» ማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ "Postscript to the Markan Secrecy Motif," *CTM* 38 (1967): 24-27 መጽሐፉ ያበቃው 16፥8 ላይ ለመሆኑ ኤፍ.ደብልዩ ዳንከር መከራከሪያ ያቀርባል፡፡ እርሱ እንደሚለው የጀመረው በድንገት እንደ መሆኑ መጠን፣ በድንገት መደምደሙ ከመጽሐፉ ጋር ይስማማል (1፥45 ጋር ያነ)፡፡ ይሁን እንጂ፣ "Can a Book End With *gar*? A note on Mark 16:8," *JTS ns* 23 (1972): 121-124 ላይ በሰዋስዋዊ ደንብ መሠረት አንድን ዓረፍተ ነገር ወይም መጽሐፍ *gar* በሚል ቃል መደምደም እንደሚቻል አመልክቷል፡፡ ጄ.ዊልያምስ ደግሞ እንዲህ ስላሉት መደምደሚያዎች አንዳንድ ገለጻዎች አቅርቧል፡፡ "Literary Approaches to the End of Mark's Gospel." *JETS* 42/1 (1999): 21-35.



እንደሚለው) እንደ ተናገሩት ከሞተ መነሣቱን አላመነችም ነበር (ዮሐ 20፥2:11-15)፡፡ ሉቃስ የሚናገረው ግን ሴቶቹን ሁሉ አስመልክቶ ነበር፡፡ በአጠቃላይ ደረጃ መላእክቱ የነገሯቸውን አምነዋል፤ ኢየሱስ ስለ ትንሣኤው አስቀድሞ መናገሩንም አስታውሰዋል (ሉቃ 24፥6-8)፡፡ ከሁለት አንዱ ለዚህ አለመጣጣም መፍትሔ ሊሆን ይችላል፡፡

በመጀመሪያ፣ ማርያም ባዶውን መቃብር እንዳየች መላእክቱ ከመገለጻቸው በፊት ቸኩላ ወጥታ ይሆናል፡፡ ስለዚህም ለጴጥሮስና ለዮሐንስ ነገረቻቸው፤ እነርሱ እየሮጡ ወደ መቃብሩ የመጡት ባዶ መሆኑን በመስማታቸው ብቻ ነበር፡፡ ሌሎቹ ሴቶች ለዘጠኙ ሐዋርያት ተናገሩ፤ ለጴጥሮስና ለዮሐንስ የተናገሩት ከዚያ በኋላ ነበር፡፡ የሆነውን ሁሉ ቢነግራቸውም ሐዋርያት መቀባዠር ስለ መሰላቸው አልተቀበሏቸውም፡፡ ማርያም ጴጥሮስና ዮሐንስን ተከትላ ወደ መቃብሩ በመሄድ አምርራ በማልቀስ ላይ እያለች ለመጀመሪያ ጊዜ መላእክቱን አየች (ዮሐ 20፥12)፡፡ ኢየሱስ የተገለጸላት ያኔ ነበር፡፡ እርግጥ ነው አምናለች፡፡ ከዚያም እየሮጠች ወደ ሐዋርያቱ በመሄድ፣ የመጀመሪያውንና በገሃድ የታየ ትንሣኤ ለመባል የሚችለውን ነገረቻቸው፡፡

ሁለተኛው ገለጻ፣ ማርያምን ጨምሮ ሴቶቹ በሙሉ መላእክቱን አዩ፤ በአንድነት ሆነውም ለሐዋርያቱ ነገሯቸው የሚለው ነው (ሉቃ 24፥9-10)፡፡ ይሁን እንጂ፣ ሁሉም አንድ ዓይነት እምነት ነበራቸው ማለት አይደለም፡፡ ይህ ደግሞ የሚጠበቅ ነው፤ ሐዋርያቱ ሁሉ በአንድ ጊዜ አልነበረም ያመኑት (ሉቃ 24፥12 እና ዮሐ 20፥8 ጋር ያነ)፡፡ ምናልባትም ማርያም ኢየሱስ ሕያው መሆኑን የሌሎቹን ያህል አላመነችም ነበር፡፡ ከአትክልቱ ስፍራ ርቃ ስትሄድ የመላእክቱን መልእክት ያህል የመቃብሩ ባዶ መሆን ግልጽ ሆነላት፡፡

ትረካው እጥር ምጥን ያለ በመሆኑ የተቀረው የታኩ ቁርጥራጭ የት እንደሚገጣጠም እንኳን ለማወቅ አይቻልም:: ቢሆንም ያን ያህል ሊያሳስበን አይገባም:: ስለሚከተሉት ጉዳዮች እርግጠኞች ለመሆን እንችላለን፤ (1) ጴጥሮስና ዮሐንስ መቃብሩ ባዶ መሆኑን የሰሙት ከማርያም ነበር፤ ወዲውኑ ወጥተው ወደ በሩ ሄዱ:: (ሌሎቹ ሴቶች የሚናገሩትን እስኪሰሙ ድረስ መቆየት ይችሉ ነበር):: (2) ኢየሱስ ከሞት መነሣቱን ከመልአኩ መስማታቸውን ሌሎቹ ሴቶች ሲናገሩ ቢያንስ ዘጠኝ ሐዋርያት ሰምተዋል:: (3) የሴቶቹ እምነት አደገ (ሉቃ 24÷8) ወንዶቹ ግን ስሜታዊነት እንዳየለባቸው አሰቡ::

ዮሐ 20÷3-10
ሉቃ 24÷12 ጋር

3ከዚያም ጴጥሮስና ሌላው ደቀ መዝሙር
ወጥተው ወደ መቃብሩ ሄዱ:: 4ሁለቱም ይሮጡ ነበር፤
ሌላው ደቀ መዝሙርም ጴጥሮስን ቀድሞት ከመቃብሩ
ደረሰ:: 5ጐንበስ ብሎ ሲመለከት ከተልባ እግር
የተሠራውን
ከፈን በዚያው እንዳለ አየ፤ ወደ መቃብሩ ግን አልገባም:: 6ይከተለው የነበረው
ስምዖን ጴጥሮስ ደረሰና ወደ መቃብሩ ገባ፤ እርሱም ከተልባ እግር የተሠራውን ከፈን
አየ፤ 7እንዲሁም በኢየሱስ ራስ ላይ ተጠምጥሞ የነበረውን ጨርቅ (እንዳለ ለብቻው
ተቀምጦ[ሱቃ]) አየ፤ ይህም ጨርቅ ከከፈኑ ተለይቶ እንደ ተጠቀለለ ነበር:: 8ከዚያም
አስቀድሞ ከመቃብሩ የደረሰው ሌላው ደቀ መዝሙር ወደ ውስጥ ገባ፤ አይቶም
አመነ፤ ([ጴጥሮስ] ግን በሆነው ነገር እየተገረመ ወደ ቤቱ ተመለሰ[ሱቃ]) 9ይኸውም
ኢየሱስ ከ[illegible] መነሣት እንዳለበት ገና ከመጽሐፍ አላስተዋሉም ነበር:: 10ከዚያም
በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ተመልሰው ወደየቤታቸው ሄዱ::

ጴጥሮስና ዮሐንስ እየተጣደፉ ወደ መቃብሩ ሄዱ:: መሮጥ የጀመሩት ሁለቱም በአንድነት ቢሆንም ጴጥሮስ ወደ ኋላ ቀረ፤ ዮሐንስ ግን የሆነውን ለማየት ጓጉቶ ስለነበር ቆሞ ሊጠብቀው አልፈለገም:: ምናልባት ጴጥሮስ ከዮሐንስ ይልቅ ሽማግሌ ስለ ሆነ ወይም በሩጫ



ደካማ ስላልሆነ ሊሆን ይችላል:: ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ጴጥሮስ ወደ ኋላ ቀርቶ ነበር:: ምስኪኗ ማርያም ግን ገና ከመቃብሩ ውጪ ነበረች:: ምናልባትም እነዚያ ሰዎች እስኪሄዱ ድረስ ወደ መቃብሩ ለመግባት አልፈለገች ይሆናል::

ዮሐንስ መቃብሩ ሥፍራ ሲደርስ፣ በእርግጥም ድንጋዩ ተንከባሎ ነበር:: መቃብሩ ደጃፍ ላይ ቆሞ ውስጥ ያለውን ለማየት ጐንበስ አለ:: የኢየሱስ በድን እዚያ አልነበረም! ያለው ኢየሱስ ተጠቅልሎበት የነበረው የከፈን ጨርቅ ብቻ ነበር:: በዚሁ ጊዜ ጴጥሮስ እያለከለከ መጥቶ ከዮሐንስ በማለፍ ወደ መቃብሩ ገባ:: ቀረብ ብሎም ተመለከተ::[14] ጴጥሮስ ከፈኑንና ኢየሱስ ራስ ላይ ተጠምጥሞ የነበረውን ጨርቅ ለብቻው ተቀምጦ አየ:: ራሱ ተጠቅልሎበት የነበረው ጨርቅ አሁንም እንደ ተጠቀለለ ነው (ሉቃ 23÷53 ጋር ያነ):: «ይህ የሚያመለክተው ጨርቁ በኢየሱስ ራስ ላይ እንደሚሆነው ጥምጥም ተደርጐ እንጂ እንደ ጠረጴዛ ጨርቅ ተጣጥፎ አለመሆኑን ነው» (Tenney p. 189):: ኢየሱስ ከውስጡ ብን ብሎ የጠፋ ይመስል ጨርቁ ፊቱ ላይ ተጠቅልሎ እንደ ነበረው ሆኖ ሳይሆን የከፈን ጨርቆቹ በሥርዓቱ ተቀምጠው እንደ ነበር ነው ጸሐፉ የሚነግረን:: አካሉን የሰረቀ ወይም ከቦታው ያነሣ ሰው ቢኖር ኖሮ ጨርቁንም ይዞ ይሄድ ነበር:: ለመሆኑ ውሎ ካደረ ሬሳ ላይ የከፈን ጨርቅ የሚፈታ ማነው? ከመቃብሩ ደጃፍ ላይ ሆነው የሚጠብቁ ወታደሮች መኖራቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት ጨርቆቹን ከአካሉ ቢፈታ እንኳ በነበሩት ሁኔታ ጠቅልሎ ለማስቀመጥ የሚደፍር አይኖርም:: ይህ በፍጹም የማይታሰብ ነው! ጴጥሮስ በጣም ተገርሟል:: በመጨረሻም ዮሐንስ እንደ ምንም ብሎ ወደ መቃብሩ በመግባት ይህን ያልተለመደ ሁኔታ አየ:: ምንም

---

[14] ከቍ. 5-8 «አየ» ለሚለው ቃል ሦስት የተለያዩ ቃላት ተጠቅሟል፤ [ቍ. 5, *blepei*; ቍ. 6, *theorei*; ቍ. 8, *eiden*] ሁሉም በአንድነት ስንወስዳቸው ዮሐንስ መቃብሩን በጥንቃቄ መረመረ የሚለውን ነው የሚስተላልፉልን::

እንኳ ከተፈጸመ ትንቢት ጋር ባያይዘው (መዝ 16፥10፤ ኢሳ 53፥10-11፤ ሆሴ 6፥1-2፤ ሉቃ 24፥26-27፤ 11፥25፤ 16፥22 ጋር ያነ)::[15] በሌላ በኩል ደግሞ ጴጥሮስ ሰፋ ያለ ጊዜና ተጨማሪ ማረጋገጫ ፈልጓል:: ግራ እንደ ተጋባ ከዚያ ሄደ:: ሁለቱ ወደየቤታቸው ሲሄዱ መንገድ ላይ ምን ያህል ተከራክረው ይሆን!

**§ 173**
**ለመግደላዊት ማርያም መታየቱ**
**([ማር 16፥9-11][16] ዮሐ 20፥11-18)**

11ማርያም ግን ከመቃብሩ ውጭ ቆማ ታለቅስ ነበር፤ እያለቀሰችም መቃብሩን ለማየት ጐንበስ አለች:: 12የኢየሱስ ሥጋ በነበረበት ቦታ፣ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት መላእክት አንዱ በራስጌ፣ ሌላው በግርጌ ተቀምጠው አየች::[16]

13እነርሱም፣ «አንቺ ሴት ለምን ታለቅሻለሽ?» ብለው ጠየቋት::

እርሷም፣ «ጌታዬን ወስደውታል፤ የት እንዳኖሩትም አላውቅም» አለች:: 14ይህን ብላ ዘወር ስትል ኢየሱስ በዚያው ቆሞ አየች፤ ኢየሱስ መሆኑን ግን አላወቀችም::

9በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን ማለዳ ከሙታን ከተነሣ በኋላ፣ ሰባት አጋንንት ላወጣላት ለማርያም መግደላዊት መጀመሪያ ታየ:: **ማር 16፥9**

ጴጥሮስና ዮሐንስ ስለ ሁኔታው ምስክርነታቸውን ለመስጠት ወደ ቤት ተመለሱ:: ማርያም መኖሯን እንኳ የዘነጉ እስኪመስሉ ድረስ ይነጋገሩ ነበር (በባሕላቸው ይህ እንዳልተለመደና አግባብነት እንደሌለው ጉዳይ አይታይም):: መቅደሱ ደጃፍ ቆማ ታለቅስ [klaio ሉቃ 8፥58፤ ዮሐ 11፥31:33] ስለ ነበር በጣም ዝላለች:: ወደ መቃብሩ ውስጥ ለማየት ጐንበስ ስትል፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ ያላዩት አስገራሚ ነገር አየች:: ምናልባት ቀደም ሲል እዚያው የነበሩት ሁለት መላእክት (ማቴ 28፥5፤ ማር 16፥5፤ ሉቃ 24፥4) የኢየሱስ ሥጋ በነበረበት ቦታ ተቀምጠው ነበር:: መላእክት ስለ መሆናቸው እርግጠኛ ነበረች:: ሉቃስ ስለ ነጭ ልብሳቸው ሲናገር፣ «እጅግ የሚንጸባርቅ» ይላል:: እንዲህ ያለው ነገር ከአእምሮ አይወጣም:: በዮሐንስ መሠረት ማርያም

[15] "The Faith of the Beloved Disciple and Community of John 20," በተሰኘ ድንቅ መጣጥፉ ውስጥ ቢ. ባይረን የተባለ ሰው በዮሐንስ 20 አወቃቀር ላይ ሰፊ ጥናት አድርጓል *JSNT* 23 (1985): 83-97:: በዚሁ መጣጥፍ ማርያም መግደላዊት (11-18) አንዳንድ ሐዋርያትና (19-23) በተለይም ቶማስ (24-29) ኢየሱስን ካዩ በኋላ ማመናቸውን አመልክቷል:: ዮሐንስ ግን ኢየሱስን ባያይም እንኳን ራሱ ተጠምጥሞበት የነበረውን ጨርቅ በማየት (ምናልባት ከአልዓዛር የተመለከተውን በማሰብ [11፥44]) ወዲያውኑ ነበር ያመነው:: ስለሆነም ኢየሱስ በተናገረው መሠረት ሳያዩ ማመንን በተግባር ያሳየ (20፥29) «የተወደደው ደቀ መዝሙር» የተባለው ዮሐንስ ብቻ ነበር:: ጠቅላላ መጽሐፉ የሚያመለክተውም ይህንኑ ነው (20፥31):: በዚህ መልኩ ዮሐንስ ለክርስቶስ ተገቢውን ምላሽ መስጠት እንደሚገባ ለአንባቢዎቹ ምሳሌ አስቀምጧል::

[16] ከቍጥር 9 እስከ ማርቆስ 16 መጨረሻ ያለው ምናልባት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉ አጨቃጫቂ ክፍሎች ዋናው ሊሆን ይችላል:: የጥንት ቅጂዎች በተለያዩ መንገዶች ነበር የተቀበሉት:: (1) ሳይናቲክ እና ባቲካነስ ገድፈውታል (ምንም እንኳ በኋላ ላይ ባቲካኑሱ ባዶ ቦታ ቢተውም):: ክሌመን፣ ኦሪገን፣ አውሳቢየስ፣ ጀሮም እና አሞነስ መገደፍ እንዳለበት ተስማምተዋል:: (2) ቫይዘንታይን፣ አሌክሳንደሪን እና ምዕራባዊ ቤተ ሰብ በሆኑ አንዳንድ ቅጂዎች ግን አካትተውታል:: (3) ሌሎች ጥቂቶች ለማስታወሻ አንዳንድ ምልክቶችን በማድረግ አካትተውታል (*f*1, 137, 138, 111[illegible] [illegible]0, 1215, 1217, 1221, 1241$^{vid}$, 1582). (4) ከቍጥር 9-20 ያሉት በአ[illegible] መደምደሚያ ተተክተዋል:: (5) ከ9-20 ያሉት ሁለቱም ቍጥሮችና አጫጭር መደምደሚያዎቹ ተካትተዋል:: አንዳንዴ ከቍጥር 9-20 መጀመሪያ ይመጣሉ፤ አንዳንዴ አጫጭሮቹ መደምደሚያዎች ይመጣሉ:: (6) በቍጥር 14 እና 15 መካከል ረዘም ያለ ጭማሪ ታክሎበታል:: ዋናው ሐሳብ ማርቆስ ይህን መጻፉን እርግጠኛ መሆን አለመቻላችን ነው:: ይሁን እንጂ፣ ሙሉ በሙሉ ብንገድፈው፣ ወንጌሉ ያልተለመደና አዳጋች ዓይነት መደምደሚያ ይኖረዋል:: ኤስ ሔልቶን፣ "Churches of Christ and Mark 16:9-20" *RestQ* 36 (1994): 33-52 ላይ አሳማኝ አማራጭ አቅርቧል:: ምናልባት ማርቆስ ራሱ ባይጽፈውም፣ አንድ ሌላ ጥንታዊ ባለ ሥልጣን ጽፎት ይሆናል፤ ስለ ሆነም እንደ ቀኖናዊ ጽሑፍ ተቀባይነት ይኖረዋል:: ስለሆነም እዚህ ላይ ማርቆስ 16፥9-20 ምንም እንኳ ማርቆስ ራሱ እንዳልጻፈው ብንቀበልም፣ እንደ ቀኖናዊ ባይሆንም ሥልጣን እንዳለው ጽሑፍ ይሆናል ማለት ነው::

እነዚህን መላእክት ስታይ ይህ የመጀመሪያ ጊዜዋ ነው:: ይህ ደግሞ መላእክቱ ለእነርሱ ከመታየታቸው በፊት ማርያም ከሌሎቹ ሴቶች በመለየት ሮጣ መጥታለች ብለን እንድናምን ምክንያት ይሆነናል:: በሌላ በኩል የሦስቱ ወንጌሎች ገለጣ መላእክቱ መጀመሪያ ሲታዩ ማርያም በቦታው የነበረች መሆኗን የሚያሳይ ይመስላል:: ስለሆነም ማርያም መላእክቱን ስታይ ይህ የመጀመሪያዋ ይሁን ወይም ለሁለተኛ ጊዜ በእርግጠኝነት ለማወቅ አንችልም::

«ለምን ታለቅሻለሽ?» በማት ማርያምን ጠየቋት:: የሚነግሯትን ብትሰማና ብታምን ኖሮ ይህ እጅግ አስደሳች ጊዜ ይሆንላት ነበር:: እነዚህ መላእክት ኢየሱስ በግልጽ የተናገረውን ለማመን ባልፈለጉ ሰዎች ጥንካሬ ሳይገረሙ አልቀሩም:: ማርያም አንድ ሰው የኢየሱስን በድን ሰርቆታል የሚለውን ሐሳብ ከአእምሮዋ ለማውጣት አልፈለገችም::

መላእክቱ መልስ ከመስጠታቸው በፊት ኢየሱስ ከማርያም ኋላ ታየ:: እርሱን ለማየት ማርያምን ወደ ኋላዋ ዘወር እንድትል ያደረጋት ምን እንደ ነበር አናውቅም:: ምናልባት መልአኩ ከማርያም በስተ ኋላ ሲመለከት፣ ወይም በጣቱ ሲያመለክታት ይሆናል:: ምናልባትም ከኋላዋ ሲራመድ የኮቴ ድምፅ ሰምታ ይሆናል:: ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ማርያም ማን መሆኑን ባታስተውል እንኳ ወደ ኋላ ዘወር ብላ አየችው:: ምናልባት በኤማሁስ መንገድ ይጓዙ በነበሩ ሁለት ሰዎች ላይ እንደ ሆነው ኢየሱስን እንዳታውቅ ዐይኖቿ ተጋርደው ይሆናል (ሉቃ 24÷16:31፤ ማር 16÷12):: ምናልባትም ዐይኖቿ በእንባ ወይም በማለዳው ጭጋግ ተጋርደው ይሆናል:: በየትኛውም ሁኔታ ገና እርሱን በቀጥታ አላየችውም (ዮሐ 20÷16)::

**ዮሐ 20÷15-18**
**ማር 16÷10 ጋር**

15እርሱም፣ «አንቺ ሴት ለምን ታለቅሻለሽ?
ማንንስ ትፈልጊያለሽ?» አላት::



እርሷም የአትክልቱ ቦታ ጠባቂ መስሎአት፣ «ጌታዬ አንተ ወስደኸው ከሆነ፣
እባክህ እንድወስደው፣ የት እንዳኖርኸው ንገረኝ» አለችው::
16ኢየሱስም «ማርያም» አላት
እርሷም፣ ወደ እርሱ ዘወር ብላ በአራማይክ ቋንቋ፣ «ረቡኒ!» አለችው፤
ትርጕሙም፣ «መምህር ሆይ» ማለት ነው::
17ኢየሱስም፣ «ገና ወደ አብ ስላላረግሁ፣ አትንኪኝ፤ ይልቁንስ ወደ
ወንድሞቼ ሄደሽ «ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ፣ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ
ዐርጋለሁ» ብሏል ብለሽ ንገሪያቸው አላት::
18መግደላዊት ማርያምም፣ ወደ ደቀ መዛሙርቱ መጥታ፣ «ጌታን አኮ
አየሁት!» አለች፤ እርሱ ያላትንም ነገረቻቸው::
11እርሱ ሕያው መሆኑንና ለእርሷም መታየቱን **ማር 16÷11**
ነገረቻቸው፤ እነርሱ ግን አላመኗትም::

«አንቺ ሴት ለምን ታለቅሻለሽ?» በማለት ኢየሱስ መልአኩ ያቀረበውን ጥያቄ አቀረበላት:: የአትክልት ቦታው ጠባቂ እንደ ሆነ ነበር ያሰበችው:: በዚያ ጠዋት ሌላ ማን ሊሆን ይችላል? ምናልባት ይህ «ውስጥ ዐዋቂ» ሊረዳት እንደሚችል ተስፋ በማድረግ ሥጋውን የት እንዳኖረው ጠየቀችው:: ከእርሱ ተቀብላ ልትወስደው እንደምትፈልግ ጭምር ተናገረች::

እርሱ ብቻ በሚጠራበት ሁኔታ ስሟን ሲጠራት ወዲያውኑ ኢየሱስን አወቀችው:: ርኅራኄና ቀረቤታው ማሰብ ከሚቻለው በላይ ነው:: «ረቡኒ» (ከፍተኛ ክብር ያለው መጠሪያ) በማለት ወደ እርሱ ተንደረደረች:: ኢየሱስ ግን እንዳትነካው (*me mou haptou*) ነገራት፤ እንዲያ ያለው ግን «እንዳታረክሰው» አልነበረም፤ ምክንያቱም ቶማስ እንዲነካው መፍቀዱ ይታወቃል (ዮሐ 20÷27):: ወደ እርሱ እንዳትቀርብ የፈለገው፣ (1) የሚቆየው ላልተወሰነ ጊዜ በመሆኑ፣ (2)

ብዙ የሚሠራ ነገር ስላለ ነው። ኢየሱስን ለማየት የመጀመሪያዋ በመሆኗ በፍጥነት ሄዳ ለሐዋርያት መንገር ነበረባት።

ኢየሱስ ለመጀመሪያ ጊዜ (ዮሐንስ ወንጌል ውስጥ) «ወንድሞቼ» አላቸው። ጊዜ እየተለወጠ ነው። የመሪነትን በትር ለእነርሱ በማስተላለፍ ላይ በመሆኑና አሁን ከኀጢአታቸው ስለ ዋጃቸው ወደ አዲስ ክብር ደረጃ ከፍ አድርጓቸዋል (ዕብ 1፥11 ጋር ያነ)። ከእንግዲህ ወንድሞች ጭምር እንጂ ወዳጆች ብቻ አይደሉም (ዮሐ 15፥15)። የኢየሱስ አቻ ጓደኞች ለመሆን አንችልም፤ ሆኖም ወንድሞቹና ከእርሱ ጋር አብረን ወራሾች ነን (ሮሜ 8፥17)። ኢየሱስ፣ «አባቴና አባታችሁ፣ አምላኬና አምላካችሁ» በሚለው ንግግሩ መካከል ልዩነት አድርጓል። ምንም እንኳ አንድ እግዚአብሔር ብቻ መኖሩ ግልጽ ቢሆንም፣ ከእርሱ ጋር ያለን ግንኙነት ኢየሱስ ካለው ግንኙነት በፍጹም የተለየ ነው። እርሱ በባሕርዩ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፤ እኛ ግን ልጆቹ የሆንነው፣ ልጆቹ አድርጎ ስለ ተቀበለን ነው። ማርያም ግራ የተጋቡት ሐዋርያት ያለቅሱ ወደ ነበረበት ቤት እየሮጠች ገባች። እርግጥ ነው፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ የተናገሩትን ሰምተዋል። አንዳንዶቹ የዮሐንስን፣ ሌሎቹ የጴጥሮስን አተረጓጐም የመቀበል ዝንባሌ አሳይተው ይሆናል። የማርያም አቋም፣ «አይቼዋለሁ! ... በእጄ ዳስሼዋሁ!» ከሚለው ከዮሐንስ ጋር ነበር። ያም ሆኖ፣ «ያው ሴት ናት»። ሊያምኗት አልፈለጉም።

### § 174
### ለሌሎች ሴቶች ታየ
### (ማቴ 28፥9-10)

9 ወዲያው ኢየሱስ አገኛቸውና «ሰላም ለእናንተ
ይሁን!» አላቸው። እነርሱም ወደ ኢየሱስ ቀርበው
እግሩን ይዘው ሰገዱለት። 10 ኢየሱስም፣ «አትፍሩ፤
ሂዱና ወደ ገሊላ እንዲሄዱ ለወንድሞቼ ንገሯቸው፤
በዚያ ያዩኛል» አላቸው።



አሁን ማቴዎስ ወደሚያቀርበው ታሪክ ተመልሰናል። ሴቶቹ ለሐዋርያቱ ለመንገር ከመቃብሩ ቦታ ሲመለሱ ኢየሱስ ተገናኛቸውና፣ «ሰላም ለእናንተ ይሁን!» አላቸው። እግሩን ይዘው ሲሰግዱለት ሳለ ወደ ገሊላ በመሄድ ያገኙት ዘንድ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲነግሩ አዘዛቸው።

ይህን ክፍል ከዮሐንስ 20፥11-18 ጋር ስናስተያየው አንድ ችግር ይገጥመናል። በዚያ ምዕራፍና ቍጥር መሠረት ኢየሱስ መጀመሪያ የታየው ከጴጥሮስና ዮሐንስ በኋላ ወደ መቃብሩ ለሄደችው ለመግደላዊት ማርያም ነበር። የማቴዎስና የዮሐንስን አቀራረብ ለማቀናጀት አንድ ወይም ሁለት ነገሮች ማድረግ ሊኖርብን ነው። በመጀመሪያ ለማለት የምንችለው ማርያም ኢየሱስን ካዩ ሴቶች ጋር አልነበረችም። እየሮጠች ወደ ሐዋርያቱ የሄደችው ብቻዋን ነበር ማለት ነው። ከጴጥሮስና ከዮሐንስ ጋር እንደ ገና ስትመለስ ከመቃብሩ ውጪ ኢየሱስ ለእርሷ ብቻ ታየ። ማርቆስ 16፥9፣ «ለማርያም መግደላዊት በመጀመሪያ ታየ» ስለሚል ኢየሱስ ለእርሷ የታየው ለሌሎቹ ሴቶች ከመታየቱ በፊት ነበር ማለት ነው። ወይም ማርቆስ 16፥9 የአቀራረብ ልዩነት አድርጓል፣ አለዚያም «መጀመሪያ» የሚለው ለማርያም መጀመሪያ መታየቱን እንጂ ለሌላ ሰው መጀመሪያ መታየቱን ለማመልከት አይደለም በማለት መተርጐም ሊኖርብን ነው።

ሁለተኛው አማራጭ ማቴዎስ 28፥9-10 የሚናገረው ኢየሱስ ለማርያምና ለማርያም ብቻ መታየቱን ነው የሚል ይሆናል። እርሷ ዋነኛ የሴቶቹ ተወካይ እንደ መሆንዋ መጠን፣ ሌሎች ሴቶችም ቢሆኑ በኋላ ኢየሱስን ማየታቸው እውነት እንደ መሆኑ መጠን ማቴዎስ ታሪኩን በማሳጠር ኢየሱስ ለሁሉም ሴቶች ጭምር መታየቱን አቅርቧል። ማቴዎስ 28፥9-10 እና ዮሐንስ 20፥11-18 ውስጥ ያለው ተጓዳኝ ሐሳብ ይህንኑ አራማጭ ያጠናክራል። ሁለቱም ወንጌሎች

ሴቶቹ እግሩን መያዛቸውን፣ መታዘዛቸውንና፣ ወንድሞቼ ማለቱን አካትተዋል::

የማቴዎስን አቀራረብ የተለየ የሚያደርገው ሌላው ነገር ለገሊላ አጽንዖት መስጠቱ ነው:: ቍጥር 10ን በማንበብ ብቻ ለሴቶቹ መታየቱን በተመለከተ በኢየሩሳሌም የታየው በዚህ ጊዜ ብቻ ነው የሚል ግምት እንዲኖረን ያደርጋል:: ይሁን እንጂ ይህ ቁጥር ሌላ ጊዜ ኢየሱስ በኢየሩሳሌም መታየቱን የሚክድ አይደለም:: ከሌሎች ተመሳሳይ ምንባቦች እንደምንረዳው ሌሎችም ነበሩ:: ይሁን እንጂ ኢየሱስ በገሊላ፣ ለእስራኤል ሁሉና እንደ ገሊላውያን ብርሃን የጀመረውን ሥራ የቀጠለ ስለ መሆኑ ማቴዎስ አጽንዖት ለመስጠት የፈለገ ይመስላል (ማቴ 4፥14-16 ጋር ያነ)::

**§ 175**
**ወታደሮቹ ለአይሁድ ባለ ሥልጣኖች መንገራቸው**
**(ማቴ 28፥11-15)**

11 ሴቶቹ በመንገድ ሳሉ፣ ከጠባቂዎቹ ጥቂቶቹ
ወደ ከተማ በመሄድ የሆነውን ሁሉ ለካህናት አለቆች
አወሩላቸው:: 12 የካህናት አለቆችም ከሽማግሌዎች ጋር
ተሰብስበው ተማከሩ፤ ለወታደሮቹ በቂ ገንዘብ በመስጠት
13 እንዲህ አሏቸው፤ «ተኝተን ሳለን ደቀ መዛሙርቱ
በሌሊት መጥተው ሰረቁት» በሉ፤ 14 ይህ ወሬ በገዢው ዘንድ ቢሰማ እንኳ እኛ
እናስረዳዋለን፤ ምንም ክፉ ነገር እንዳይደርስባችሁ እናደርጋለን:: 15 ወታደሮችም
ገንዘቡን ተቀብለው እንደ ታዘዙት አደረጉ:: ይህም ታሪክ እስከ ዛሬ በአይሁዶች ዘንድ
በሰፊው እንደ ተሰራጨ ነው::

ሴቶቹ ሪፖርታቸውን ሲያቀርቡ ሳለ ጠባቂዎቹም የራሳቸውን ሪፖርት ማቅረብ ነበረባቸው:: እነዚህ ሮማውያን ወታደሮች ከባድ ችግር ገጥሟቸዋል:: ያመለጠ እስረኛን ቅጣት መቀበላቸው የማይቀር ነው:: ስለዚህ ወደ ጲላጦስ ከመሄድ ይልቅ ሬሳው የራሳቸው ወገን ወደሆነው የካህናት አለቆች ሄዱ:: እነዚያ አይሁውያን ባለ ሥልጣኖች ነገር የሚገባቸው ዓይነት ነበሩ:: ዕቅዳቸው ግን አደገኛ ነው::



ጠባቂዎቹ ሥራ ላይ እያሉ እንቅልፍ እንደ ወሰዳቸው ከተናገሩ ያለ ጥርጥር ይገደላሉ:: ኢየሱስ «እንዲያመልጥ» ማድረጋቸው ራሱም ከዚያ ያላነሰ ቅጣት ማምጣቱ ግልጽ ነበር:: ሁለቱም አማራጮች የሚመረጡ አይደሉም:: በእጃቸው ሙሉ ያፈሱት ገንዘብ ምናልባት «ትክክለኛ» ምርጫ እንዲያደርጉ ይረዳቸው ይሆናል:: ምናልባት ጲላጦስ ስለዚህ ጉዳይ ቢሰማ እንኳ ነገሩን እንደሚያበርዱት የካህናቱ አለቆች ቃል ገቡላቸው:: የአርብ ዕለቱን ጉዳይ ግምት ውስጥ በማስገባት ስንመዝነው ይህን ለማድረግ ብቃት ይኖራቸዋል:: የኢየሱስ በድን ተሰርቆ የመወሰዱ ታሪክ ማቴዎስ በነበረበት ዘመን ሁሉ በመሠራጨት ላይ ነበር:: አንዳንዶች ዛሬም እንኳ ያን ሐሳብ ያቀርባሉ:: ግን፣ ምን ያህል አሳማኝ ነው? ኢየሱስ ከሞት መነሣቱ ቢነገራቸው እንኳ ደቀ መዛሙርቱ አላመኑም ነበር:: ታዲያ፣ ያላመኑትን ለማድረግ ለምን ብለው ሬሳ ይሰርቃሉ? ሐሰት መሆኑን ልባቸው ለሚያውቀው ነገር ለምን ብለው በሰማዕትነት ይሞታሉ?

ኢየሱስ ለአንድ አይሁዳዊ በሚደረግለት ዓይነት በክብር የተቀበረ መሆኑን መረዳት አለብን፤ 100 ሊትር ሽቱና ቅመማ ቅመም ባለ ጸጋ ሰው መቃብር ላይ ነበር የሚደረገው:: ከዚህ የተለየ ቀብር ግን ዝቅተኛ ነው:: ከዚህም ሌላ የሞተ ሰውን አካል ካረፈበት ቦታ ማንቀሳቀስ ለሟቹም ሆነ ያን ለሚያደርግ ሰው እንደ ታላቅ ርኩሰት ነበር የሚቈጠረው:: ከኢየሱስ ወዳጆች አንዱም እንኳ እንደዚያ አያደርግም፤ ጠላቶቹም ቢሆኑ እንደዚያ ማድረግ አይፈልጉም:: በሌላም በኩል የታጠቁ ጠባቂዎች በሥፍራው ነበሩ:: ደቀ መዛሙርቱ መቃብር ቆፍረው በድኑ የተጠቀለለበትን ናይለን ጨርቅ ይፈታሉ ማለት ዘበት ነው፣ በፍራቻ በራቸውን ዘግተው ተቀምጠዋል (ዮሐ 20፥19):: በጣም አስቂኝ የሚሆነው ደግሞ ጠባቂዎቹ ደቀ መዛሙርቱን ተጠያቂ ማድረጋቸው ነበር:: ለመሆኑ፣ ተኝተው ከነበረ እንዴት አወቁ? ተኝተው ካልነበረስ ለምን አላስቆሟቸውም? ደቀ መዛሙርቱ በስርቆት

ያልተከሰሱት ለምንድ ነው? ይህ አስተሳሰብ ምክንያታዊም፣ የሚታመንም አይደለም:: ከ50 ቀን በኋላ በዚያው ከተማ 3000 ሰዎች ክርስቶስ እግዚአብሔር መሆኑን አምነው የተቀበሉት በዚህ ምክንያት ነበር::

**§ 176**
**በኤማሁስ መንገድ ለነበሩ ሁለት ሰዎች መታየቱ**
**([ማር 16፥12-13] ሉቃ 24፥13-32)**

ወንጌሎቹ የሚያቀርቡት ታሪክ እውነተኛ ብቻ አይደለም፤ ጥልቅ መንፈሳዊ መልእክት ያለውና ትእምርታዊም ነው::[17] በመጀመሪያ፣ ከትንሣኤው በኋላ ኢየሱስ መታየቱን ያረጋግጣል:: ሁለት፣ «ሕጋዊ» ምስክሮች አሉን፤ (ሉቃ 24፥4 ጋር ያነ)፤ ድንግዝግዝ ያለው ሁኔታና ኀዘን ወደ ደስታ መለወጡ፣ ትንቢት መፈጸሙና ለሐዋርያት መነገሩ:: ሁለተኛ፣ ለብሉይ ኪዳን ሥር ነቀል ለውጥ መስጠቱ (ለምሳሌ ትምህርተ ክርስቶስን አስመልክቶ):: አዲስ ኪዳን ብሉይ ኪዳንን የሚመለከትበት መንገድ እንደ ተራ ሥነ ጽሑፋዊ ፈጠራ አይሆንም:: ከትንሣኤው በኋላ ኢየሱስ ባቀረበው ትምህርት ጸሐፊዎቹ ይህን ተምረዋል::

**ሉቃ 24፥13-16**
**ማር 16፥12 ጋር**

13በዚሁ ቀን ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱ፣ ከኢየሩሳሌም ዐሥራ አንድ ኪሎ ሜትር ያህል ወደሚርቅ፣ ኤማሁስ ወደሚባል መንደር ይሄዱ ነበር፤
14እነርሱም ስለ ሆነው ነገር እርስ በርስ ይነጋገሩ ነበር:: 15እየተነጋገሩና እየተወያዩ ሳለም ኢየሱስ ራሱ
ቀርቦ ከእነርሱ ጋር ይሄድ ጀመር፤ (በሌላ መልክ ታያቸው[ማር]) 16ነገር ግን
እንዳያውቁት ዐይናቸው ተይዞ ነበር::

[17] "The Place of Emmaus Story in Luke - Acts," *NTS* 30 (1984): 481-497 ላይ ጸሐፊው ጉዞ፣ ትንቢት፣ ማወቅና በተለይም ማስተናገድ የተሰኙት ሉቃስ የሚያዘወትራቸው ዐበይት ሐሳቦች ታሪኩ ውስጥ ያላቸውን ጉልህ ስፍራ ያመለክታል::



ነገሩ የጀመረው እሑድ ከሰዓት በኋላ ከሁለቱ አንደኛው ቀልዮጳ[18] ተብሎ ቢጠራ እንኳ ስማቸው ያልታወቀ[19] ሁለት ደቀ መዛሙርት ከኢየሩሳሌም ዐሥራ አንድ ኪሎ ሜትር ያህል ወደምትርቅ[20] ኤማሁስ ወደሚሏት ትንሽ መንደር በሚጓዙበት ጊዜ ነበር::

እዚህ ላይ ሁለት ነገሮች በጉልህ ተቀምጠዋል:: ይሄዱ ነበር እና ይነጋገሩ ነበር የተሰኙት በምንባቡ ውስጥ በተለያዩ የግሪክ ቃላት ተገልጸዋል:: ሁለቱ ደቀ መዛሙርት እያዘኑ ወደ ቤታቸው በመሄድ ላይ ሳሉ፣ በቅርብ ስለ ሆነው ጉዳይ ይነጋገሩ ነበር:: ሁለቱም ከኢየሱስ ተከታዮች ጋር የጠበቀ ቀረቤታ ነበራቸው:: እንደ እውነቱ ከሆነ እንደ «ጓደኞቻቸው» ጴጥሮስና ዮሐንስ ሁሉ በዚያ ማለዳ (ቊ 22-24) ሴቶቹ የተናገሩትን ሰምተዋል:: ምናልባትም ከይሁዳ አገልግሎቱ አንስቶ በድል እስከ መግባቱ ድረስ ኢየሱስን ሳይከተሉት አልቀሩም:: ከፍተኛ ተስፋ ሰንቀው ነበር:: አሁን ግን በዚህ ታላቅ ነቢይ መገደል የነበራቸው ተስፋ እልም ብሎ ጠፍቷል:: የአይሁድ መሪዎች በኢየሱስ ላይ ያደረጉት ጭካኔ የጥንቶቹ ወገኖቻቸው በታላላቅ የእግዚአብሔር

[18] አውሳቤዎስ (*Ecclesiastical History*, 3.11) ቀለዮጳ የዮሴፍ ወንድም መሆኑን ይናገራል፤ ስለ ሆነም፣ በጋብቻ የኢየሱስ አጎት ነው ማለት ነው:: ቀለዮጳ ከሚለው ለየት ያለ አጠራር ቢሆንም፣ የግድ ዮሐንስ 19፥25 ውስጥ የተጠቀሰው ቀልዮጳ ነውማለት አይደለም::

[19] አንዳንዶች ይህ ሰው ያልተጠቀሰ ደቀ መዝሙር በኤማሁስ ይኖር የነበረው ሉቃስ ራሱ ነው በማለት ይገምታሉ:: ምንም እንኳ አራቱ ወንጌሎች የጸሐፊዎቻቸው አሻራ እንዳረፈባቸው ይህ ቢመለክትም፣ እንዲህ ለማለት ግን አሳማኝ ማስረጃ የለም:: ይሁን እንጂ ሉቃስ የትንሣኤው ምስክር መሆኑን በእርግጠኝነት እንናገራለን:: ማስረጃዎቹ አስተማማኝ በመሆናቸው፣ የሕክምና ባለሙያውና ግሪካዊው ሉቃስ ኢየሱስ በአካል ከሞት ስለ መነሣቱ እርግጠኛ ሆኗል::

[20] ኤማሁስ የት ስለ መሆኑ ከአራት የማያንሱ ሐሳቦች ቀርበዋል፤ ከሞላ ጐደል ሁሉም ከኢየሩሳሌም ተመሳሳይ ዓይነት ርቀት ነበራቸው:: ሰፋ ላለ ማብራሪያ የW.L. Liefeld, "Exegetical Notes: Luke 24:13-35," *TrinJ* 2 *ns* (1981): 223-229 ይመለከቷል::

ነቢያት ላይ ያደረጉትን ነው:: እነዚህ ሁለቱ ግን በጣም የበለጠውን ማለት መሲሑን ጠብቀው ነበር::

እንደ ንግግራቸው ሁሉ እርምጃቸውም ቀስስተኛ ቢሆንም ለመድረስ የሚፈልጉበት ሁነኛ ቦታ ነበራቸው:: ሐሳብ በመለዋወጥ ላይ ሳሉ [*antiballo*] ምንም ሳያስቡ ኢየሱስ ተቀላቀላቸው (ቃል በቃል፣ «እንዳያውቁት ዐይናቸው ተይዞ ነበር»):: ይህ ዐይኖቻቸውን ጋርዶት የነበረው እግዚአብሔር መሆኑን የሚመለክት የአጻጻፍ መንገድ ነበር:: ኢየሱስ በተለየ መልኩ ታያቸው የሚለው የማርቆስ አባባል ይህን አተረጓጎም ይደግፋል::

**ሉቃ 24÷17-24**

17እርሱም፣ «እየሄዳችሁ መንገድ ላይ እርስ
በርስ እንዲህ የምትወያዩት ምንድን ነው?» አላቸው::
እነርሱም በሐዘን ክው ብለው ቆሙ::
18ከእነርሱም አንዱ ቀለዮጳ የተባለው፣ «በእነዚህ ቀናት እዚህ በኢየሩሳሌም የሆነውን
ነገር የማታውቅ፣ አንተ ብቻ ለአገሬ እንግዳ ነህን?» ሲል መለሰለት::
19እርሱም፣ «የሆነው ነገር ምንድን ነው?» አላቸው::
እነርሱም እንዲህ አሉት፤ «በእግዚአብሔርና በሰው ሁሉ ፊት በተግባርና
በቃል ብርቱ ነቢይ ስለ ነበረው ስለ ናዝሬቱ ኢየሱስ ነው፤ 20እርሱን የካህናት
አለቆችና ገዦቻችን ለሞት ፍርድ አሳልፈው ሰጡት፤ ሰቀሉትም:: 21እኛ ግን
እስራኤልን ይቤዠል ብለን ተስፋ ያደረግነው እርሱ ነበር፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ፣ ይህ
ከሆነ ዛሬ ሦስተኛው ቀን ነው:: 22ደግሞም ከእኛው መካከል አንዳንድ ሴቶች
አስገረሙን፤ እነርሱም ማለዳው ወደ መቃብሩ ሄደው ነበር፤ 23ሥጋውንንም ባጡ
ጊዜ መጥተው እርሱ በሕይወት እንዳለ የነገሯቸውን መላእክት በራእይ እንዳዩ
አወሩልን:: 24ከእኛም መካከል አንዳንዶች ወደ መቃብሩ ሄደው፣ ልክ ሴቶቹ
እንዳሉት ሆኖ አገኙት፤ እርሱን ግን አላዩትም::»

የሆነው ነገር ምን እንደ ነበር ሲጠይቃቸው ክው ብለው ከመደንገጣቸውም በላይ በእርሱ ቸልተኝነት ተገርመዋል:: እንዲያውም



በጣም በመደንገጣቸው በነበሩበት ቦታ ቆሙ:: «ለመሆኑ አንተ የምትኖረው በዚህ አገር አይደለም እንዴ?» የሚል ጥያቄ በማቅረብ ዝምታውን የሰበረ ቀለዮጳ ነበር:: ኢየሱስም ብዙ ሊያነጋግር በሚችል ሁኔታ፣ «የሆነው ነገር ምንድን ነው?» በማለት ጠየቀ:: እነርሱም ስለ እርሱና እርሱን አስመልክቶ ስለ ነበራቸው ተስፋ ለኢየሱስ ነገሩት:: ኢየሱስ ከናዝሬት የመጣ ነቢይና (ሉቃ 4÷24 ጋር ያነ) ታላቅ ተአምር አድራጊ ሰው መሆኑን ተገንዝበዋል:: እንዲያውም እስራኤልን ይቤዠል ብለው ጠብቀውት ነበር (ሉቃ 1÷68 ጋር ያነ):: ሆኖም እርስ በርሱ የሚጋጭ በሚመስል መልኩ ኢየሱስ ስለ ፈጸመው ቤዛነት መንም ሐሳብ አልነበራቸውም::

ሦስት ቀን ሆኖታል:: ለአይሁድ ይህ ሁነኛ ፋይዳ ያለው ነው:: የሞተው ሰው መንፈስ ለሦስት ቀን ያህል በበድኑ ዙሪያ ካንዣበበ በኋላ እንደሚሄድ ያምኑ ነበር:: አሁን ኢየሱስ ጨርሶ ሄዷል:: በተጨማሪም ይቤዠል ብለው በጠበቁት ሰው ሞት በማዘን ላይ ሳሉ አንድ ያልታወቀ ሰው ሥጋውን ሰርቆ ወስዶታል:: ይህ በራሱ በቂ ያልሆነ ይመስል ሴቶቹ የተለየ ታሪክ ይዘው መጥተዋል:: ኢየሱስ ሕያው መሆኑን መላእክት እንደነገሯቸው በመግለጽ ላይ ነበሩ:: ጴጥሮስና ዮሐንስም መቃብሩ ባዶ መሆኑን ቢያረጋግጡም መላእክትን ወይም ሕያውም ሆነ ሙት ሌላ ማንንም አላዩም::

**ሉቃ 24÷25-32**

25እርሱም እንዲህ አላቸው፤ «እናንተ
የማታስተውሉ ሰዎች፤ ልባችሁም ነቢያት የተናገሩትን
ሁሉ ለማመን የዘገየ፣ 26ክርስቶስ ይህን መከራ
መቀበልና ወደ ክብሩም መግባት አይገባውምን?»
27ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ በቅዱሳ መጻሕፍት ስለ
እርሱ የተጻፈውን አስረዳቸው::

28ወደሚሄዱበትም መንደር በተቃረቡ ጊዜ፣ ኢየሱስ አልፎ የሚሄድ መሰለ::
29እነርሱ ግን፣ «ምሽት እየተቃረበ፣ ቀኑም እየመሸ ስለ ሆነ ከእኛ ጋር እደር»
ብለው አጥብቀው ለመኑት፤ ስለዚህ ከእነርሱ ጋር ለማደር ገባ::
30ከእነርሱ ጋር በማእድ በተቀመጠ ጊዜ እንጀራውን አንሥቶ ባረከ፤
ቈርሶም ሰጣቸው:: 31በዚህ ጊዜ ዐይናቸው ተከፈተ፤ ዐወቁትም፤ እርሱም ከእነርሱ
ተሰወረ:: 32እነርሱም፣ «በመንገድ ሳለን፣ እያነጋገረን ቅዱሳት መጻሕፍትንም ገልጦ
ሲያስረዳን፣ ልባችን እንደ እሳት ይቃጠልብን አልነበረምን?» ተባባሉ::

ቀለዮጳ ማኅበራዊ ግንኙነቱ ደካማ በመሆኑ ኢየሱስን ወቀሰው:: ኢየሱስ ደግሞ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመረዳት ደካማ በመሆናቸው ሁለቱንም ወቀሰ:: ከብሉይ ኪዳን ደስ የሚላቸውን ብቻ እየመረጡ በማንበባቸው እንደ መዝሙር 22 እና ኢሳይያስ 53 የመሳሰሉ ክፍሎችን በቸልታ አልፈዋቸዋል:: ከሌሎቹ ጉዳዮች መካከል ትንሣኤና ዕርገቱንም በማካተታቸው እነዚህ ምንባቦች ለኢየሱስ በጣም አስፈላጊ ናቸው (ፊልጵ 2÷6-11 ጋር ያነ)::

በመንገዝ ላይ ሳሉ ምንባቦቹ በምን ዓይነት ሁኔታ ስለ መሲሑ እንደተናገሩ እየጠቀሰ ብሉይ ኪዳንን ሁሉ («በሙሴና በነቢያት» አማካይነት በአጭሩ በቀረበው መሠረት) አብራራላቸው:: ኤማሁስ ሲደርሱ ኢየሱስ አልፎ የሚሄድ መሰለ:: እንዲህ ሲባል ሊያታልላቸው ይሞክር ነበር ማለት አይደለም:: ይህ የተለመደ ማኅበራዊ ሁኔታ ነበር:: ባለቤቱ እንግዳውን ይጋብዘዋል፤ እንግዳው ደግሞ ላለመቀበል ያንገራግራል:: ባለቤቱ እንግዳውን እንዲቆይ ይጋብዘዋል፤ እንግዳው ግን የለም፣ እሄዳለሁ ይላል:: ባለቤቱ ጫን አድርጐ እንዲቆይ ከጠየቀው እንግዳው ይቀበላል::[21] በዚህ ሁኔታ ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር

[21] «አጥብቀው ለመኑት» [*parebiasanto*] ተብሎ የተተረጐመው ግሥ፣ «አስገደዱት» ሊባል ይችላል:: ይህን ስለ መሰለው «አስገዳጅ» ግብዣ ዘፍ 24÷55፤ መሳ 19÷9፤ ጦቢ: 10÷8፤ ሐሥ 16÷15 ይመ::



እንዲያድር አደረጉት:: የዐሥራ አንድ ኪሎ ሜትር ጕዞአቸው ያበቃው በዚያ ቀን ምሽት ላይ ነበር::

ማእድ ላይ ተቀምጠው ሳለ ኢየሱስ የባለቤት ወይም የአስተናጋጅን ስፍራ ያዘ:: «እንጀራውን አንሥቶ ባረከ፤ ቈርሶም ሰጣቸው»:: እንደዚያ በሚያደርግበት ጊዜ እርሱ መሆኑን እንዲያውቁ ያደረጋቸው አንዳች የተለየ ነገር ነበረ:: አንዳንዶች ወዲያውኑ ያወቁት በጌታ እራት ላይ ነበር ይላሉ:: ይሁን እንጂ ሰዎቹ የጌታን እራት የሚካፈሉበት ምክንያት አልነበራቸውም:: እንዲያውም ባለፈው ሐሙስ ምሽት ሰገነቱ ላይ ከእርሱ ጋር ስላልነበሩ ስለ ጌታ እራት የሚያውቁት ነገር ላይኖራቸው ይችላል:: ከዚህም በላይ መንግሥቱ እስኪመሠረት ድረስ ከእንግዲህ በዚህ ሥርዐት ተሳትፎ እንደማይኖረው ኢየሱስ ተናግሮ ነበር:: ሌላው ሐሳብ ደግሞ የቈሰሉ እጆቹን አይተዋል የሚል ነው:: አሁንም ሌላው ሐሳብ ኢየሱስ የጸለየበትና እንጀራውን ያካፈለበት መንገድ የተለየ ነበር ይላሉ (ሉቃ 9÷10-17 ጋር ያነ):: እነዚህ እውነት ሊሆኑ ቢችሉም፣ ዐይናቸው እንዲያዝ እንዳደረገ ሁሉ እግዚአብሔር ዐይናቸውን ከፈተ ስለዚህ እርሱን ማወቃቸው የእግዚአብሔር ሥራ ነበር ማለት ይቻላል::[22]

ኢየሱስ ምስጢራዊ በሆነ ሁኔታ ከእነርሱ ተሰወረ:: ነገሮች ሁሉ ቦታ ቦታቸውን ያዙ:: ወደ ኤማሁስ ሲጓዙ ኢየሱስ ቅዱሳት መጻሕፍትን ሲብራራላቸው፣ «ልባቸው ይቃጠልባቸው» እንደ ነበር አስታወሱ (ሉቃ 12÷35፤ ዮሐ 5÷35 ጋር ያነ):: «አዎን፣ በእርግጥ ኢየሱስ ራሱ ነው» ብለው ይሆናል:: «እንደዚያ የሚያስተምር እርሱ ብቻ ነው፤ ቀደም ብለን ማወቅ ነበረብን»::

[22] እዚህም ላይ በመለኮታዊ አሠራር መሠረት፣ «ዐይናቸው ተከፈተ» ማለት ይቻላል::

### § 177
### ሁለቱ ለዐሥሩ ተናገሩ
**(ሉቃ 24፥33-35፤ 1ቆሮ 15፥5 ጋር ያነ)**

33በዚያኑም ሰዓት ተነሥተው ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፤ ዐሥራ አንዱና ከእነርሱ ጋር የነበሩትም በዚያ በአንድነት ተሰብስበው አገኟቸው፤ 34እነርሱም «ጌታ በእርግጥ ተነሥቷል! ለስምዖንም ታይቶአል» ይባባሉ ነበር:: 35ሁለቱ ደቀ መዛሙርትም በመንገድ ላይ የሆነውንና ኢየሱስ እንጀራውን በቈረሰ ጊዜ እንዴት እንዳወቁት ተረኩላቸው::

ጊዜው በምሽት መጀመሪያ ላይ ነበር:: ቀለዮጳና ጓደኛው ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ ላይ ናቸው:: ዐሥራ አንዱን ኪሎ ሜትር በአጭር ጊዜ ነበር ያገባደዱት:: ሐዋርያቱ ተደብቀው ወደ ነበረበት ቦታ ለመድረስ በኢየሩሳሌም አደባባዮች ሲያልፉ ጊዜው እየመሸሸ ነበር:: ቦታውን ያውቃሉ፤ ያንለት ማለዳ እዚያ ነበሩ::

ሐዋርያቱ፣ «ዐሥራ ሁለቱ» በመባል ይጠሩ ነበር፤ አሁን ግን ይሁዳ ከእነርሱ በመለየቱና በመሞቱ፣ «ዐሥራ አንዱ» ተብለዋል:: ሉቃስ ስለ ሐዋርያቱ ስብሰብ በሚናገርበት ጊዜ በዚህ አዲስ መጠሪያ ይጠቀማል:: ዮሐንስ ያግሞ በቦታው የነበሩት ዐሥር ብቻ መሆናቸውን ነው የሚያመለክተው (ቶማስ ግልጽ ባልሆነ ምክንያት ከእነርሱ ጋር አልነበረም):: ስለ ቶማስ የማያውቁ አንባቢዎችን ግራ ላለማጋባት ሲል ሉቃስ ዝርዝር ነገሩን ትቶታል፤ በኋላ ይህን የጻፈው ዮሐንስ ነው:: (ጳውሎስም በ1ቆሮ 15፥5 ስለ ሐዋርያቱ ስብሰብ ሲናገር ይህንኑ ነበር ያደረገ... ትክክለኛ ቊጥራቸው ዐሥራ አንድ ቢሆንም ዐሥራ ሁለቱ ብሏቸዋል)::

ቀለዮጳና ጓደኛው በሚናገሩት ታሪክ ምናልባት ተቃውሞ ሳይገጥማቸው እንደማይቀሩ ሳያስቡ አልቀሩም:: በጣም ደስ የሚለው ግን፣ ጴጥሮስም ኢየሱስን በማየቱ ምስክርነቱን ሰምተው ነበር:: ኢየሱስ የታየ ስለ መሆኑ እርሱ ቢያንስ ሦስተኛ ግለ ሰብ መስካሪ



መሆኑ ነው:: ኢየሱስ ለጴጥሮስ የታየው መቼና የት እንደ ነበር አናውቅም:: ይህን በግል ማድረጉ ኢየሱስ ምን ያህል ቸር መሆኑን ያመለክታል:: ጴጥሮስ ቀያፋ ግቢ ውስጥ ኢየሱስን በመካዱ አሁንም ቢሆን ጸጸት ነበረበት::

### § 178
### ለዐሥሩ መታየቱ
**([ማር 16፥14] ሉቃ 24፥36-43 ዮሐ 20፥19-25)**

ሉቃ[24]36ይህን እየተነጋገሩ ሳሉ፣ (በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን በምሽት አይሁድን በመፍራት በሮቹን ቈልፈው ተሰብስበው ሳለ[ዮሐ]) ኢየሱስ ራሱ በመካከላቸው ቆሞ፣ «ሰላም ለእናንተ ይሁን» አላቸው::

37እነርሱ ግን ደንግጠው በፍርሀት ተዋጡ፤ መንፈስም ያዩ መሰላቸው:: 38(ከተነሣ በኋላ ያዩት ሰዎች የነገሯቸውን ስላላመኗቸው፣ አለማመናቸውንና የልባቸውን ደንዳኔ ነቀፈ[ማር]) እርሱም እንዲህ አላቸው፤ «ለምን ትጨነቃላችሁ? ለምንስ ጥርጣሬ በልባችሁ ይገባል? 39እጆቼንና እግሮቼን ተመልከቱ፤ እኔው ራሴ ነኝ:: ደግሞም ንኩኝና እዩ፤ በእኔ እንደምታዩት መንፈስ ሥጋና ዐጥንት የለውምና::»

40ይህንም ብሎ እጆቹንና እግሮቹን አሳያቸው:: 41እነርሱም ከመደሰትና ከመገረም የተነሣ ገና ሳያምኑ፣ «በዚያ ቦታ አንዳች የሚበላ ነገር አላችሁን?» አላቸው:: 42እነርሱም ከተጠበሰ ዓሣ ጋር አንድ ቁራሽ ሰጡት፤ 43እርሱም ተቀብሎ በፊታቸው በላ::

ሐዋርያቱ የምሽት ምግባቸውን ለመመገብ ተቀምጠው ሳለ በእነዚያ በጣም በተደነቁ ሁለት ደቀ መዛሙርት ሁኔታ መመገባቸውን አቋረጡ:: ተረጋግተው እንደ ገና እንደ ተቀመጡ፣ አሁንም መመገባቸውን አንድ ገና አቋረጡ:: በዚህ ጊዜ በር ማንኳኳትም ሆነ ቁልፍ መከፈት አልነበረም:: ድንገት እዚያ ተገኘ! ኢየሱስ በቀላሉ ግድግዳውን አልፎ የመጣ መሰለ:: በእርግጥም ነበር፤ በባሕር ላይ ለመሄድ ከቻለና በሥጋዌው ወራት ራሱን መለወጥ ከቻለ፣ በትንሣኤ አካሉ ግድግዳን ማለፍና በአንዳንድ ሁኔታ «በግዝፈት» መገለጥ መቻሉ

አስደንጋጭ አይሆንም:: ቀለል ያለ ሰላምታ በማቅረብ ትኩረታቸውን ሳበ:: ደቀ መዛሙርቱ መፍራትና መደንገጣቸው ግልጽ ነበር::

ኢየሱስ ስለ አለማመናቸው ገሠጻቸው:: እፊታቸው ቆሞ እንኳ መንፈስን እንዳዩ ነበር የሚያስቡት:: ምንም እንኳ ማመናቸውን ቢናገሩም (ሉቃ 24÷34) አሁን ማረጋገጫ ይፈልጋሉ:: እንዲህ የሆነው በተለያየ የእምነት ደረጃ ላይ በመኖራቸው ነው ቢባል አግባብነት ይኖረዋል:: አንዳንዶች በሚገባ አምነዋል፤ አንዳንዶቹ ገና ይቀራቸዋል:: ኢየሱስ ሕያው መሆኑን ሴቶቹ ሲነግሯቸውም ተጠራጥረው ነበር:: ምናልባትም ኢየሱስን ሳያይ በትንሣኤው ያመነ ዮሐንስ ብቻ ነበር (ዮሐ 20÷8):: ማናቸውም ቢሆኑ ኢየሱስን ማየት አያስፈልጋቸውም ነበር:: ሴቶቹም ሆኑ መላእክቱ እንዲናገሯቸው አያስፈልጋቸውም ነበር:: ኢየሱስ እንደ ገና እንደሚነሣ ነግሯቸዋል (ማቴ 12÷40፤ 16÷21፤ 17÷9፤ 17÷22-23፤ 20÷18-19፤ 26÷32፤ ማር 14÷28፤ ዮሐ 2÷19-22):: ያ ብቻ ይበቃቸው ነበር::

ምንም እንኳ መንፈስ እንዳልሆነ እንዲያረጋግጡ ኢየሱስ እጆቹንና እግሮቹን ቢያሳያቸውና እንዲዳስሱትም ቢፈቅድላቸው (1ዮሐ 1÷1 ጋር ያነ) አሁንም የማመን ችግር ነበረባቸው:: እጅግ ደስ ብሏቸዋል፤ እጅግም ተገርመዋል:: ማመን ስላልቻሉ እንጂ፣ ማመን ስላልፈለጉ አልነበረም ያላመኑት:: በሌላ አነጋገር ገና ውስጣቸው አልዘለቀም:: ስለዚህም ለእራት ያቀረቡትን የተጠበሰ ዓሣ እየበሉ ኢየሱስ ለአንዴና ለመጨረሻ ሐቁን ግልጽ አደረገላቸው:: አሁን ሁሉም ግልጽ ሆኖላቸዋል:: ያለ ምንም ጥርጥርና ለመካድ በማይቻልበት ሁኔታ በአካል ሕያው ሆኗል!

ዮሐ 20÷20-23

[20]ደቀ መዛሙርቱም ጌታን ባዩት ጊዜ እጅግ ደስ አላቸው::



[21]ኢየሱስም እንደ ገና፣ «ሰላም ለእናንተ ይሁን፤ አብ እኔን እንደ ላከኝ እኔም እናንተን እልካችኋለሁ» አላቸው:: [22]ይህን ካለ በኋላም፣ እፍ አለባቸውና እንዲህ አላቸው፤ «መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፤ [23]የሰዎችን ኀጢአት ይቅር ብትሉ፣ ኀጢአታቸው ይቅር ይባልላቸዋል፤ ኀጢአታቸውን ይቅር ባትሉ ግን፣ ይቅር አይባልላቸውም::»

«ልጆች፣ እስቲ አሁን ወደ ዋናው ጉዳይ እንሂድ» በሚል መልክ ኢየሱስ «ሰላም ለእናንተ ይሁን» አላቸው:: በዋነኛነት ደረጃ የመጣው ሕያው መሆኑን ሊያሳያቸው አልነበረም:: ድጋሚ ተልዕኮ ሊሰጣቸው ነው:: «አብ እኔን እንደ ላከኝ፣ እኔም እናንተን እልካችኋለሁ» ማለቱ ከሦስት ቀን በፊት የፋሲካን እራት ይበሉ በነበረ ጊዜ ኢየሱስ የነገራቸውን ብዙ ነገሮች ሊያስታውሳቸው ይገባል (ዮሐ 14÷2-5:18-19፤ 15÷20-27፤ 16÷5-7:16-23):: ኢየሱስ ላይ እንደ ደረሰ ሁሉ እነርሱም ላይ ተቃውሞና ስደት ሊደርስባቸውና ሊያሳስባቸው ይችላል:: መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክ የሰጠውን ተስፋ ሊያስታውሳቸው ይችላል:: እንደ ገና ወደ አብ የመመለሱን መራር እውነት ሊያስታውሳቸውም ይሆናል:: ከሚገባ በላይ ከእርሱ ጋር መቀራረብ የለባቸውም፤ አስቀድሞ ስለዚህ ጊዜ ተናግሮ ነበር::

> ከደቀ መዛሙርቱም አንዳንዶቹ፣ «ከጥቂት ጊዜ በኋላ አታዩኝም፤ ይሁን እንጂ፣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ ታዩኛላችሁ» እንዲሁም፣ «ወደ አብ እሄዳለሁ» ሲል ምን ማለቱ ነው? ተባባሉ:: እውነት እላችኋለሁ፤ እናንተ ታለቅሳላችሁ፤ ታዝናላችሁም፤ ዓለም ግን ሐሤት ያደርጋል፤ ይሁን እንጂ ሐዘናችሁ ወደ ደስታ ይለወጣል (ዮሐ 16÷17:20)::

ከዚህ አጭር ተልእኮ በኋላ ኢየሱስ እፍ አለባቸውና፣ «መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ» አላቸው:: ይህ የተስፋው መፈጸም ምሳሌያዊ

ማሳሰቢያ ነበር:: ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ የሚመጣው ኢየሱስ ወደ አብ ሲያርግ ብቻ ነው (ዮሐ 7÷39፤ 16÷7):: አሁን ግን ደቀ መዛሙርቱ ላይ እፍ በማለት ወደ ፊት የሚሆነውን የመንፈስ ቅዱስ መምጣት የሚወክል ነገር ማድረጉ ነበር::[23] «እስትንፋስ» እና «መንፈስ» የሚሉት ቃላት በዕብራይስጥም ሆነ በግሪክ አንድ ዓይነት ትርጉም ነው ያላቸው:: ስለሆነም እንዲህ የማድረጉ ትርጉሙ ለዐሥራ አንዱ ግልጽ ነበር:: ምናልባትም እግዚአብሔር በአዳም ሕይወት/መንፈስን እፍ እንዳለበት ከሚያመለክተው ከዘፍጥረት 2÷7 ጋር ሳያያይዙት አልቀረም:: ሐዋርያቱ ተልእኮአቸውን በሚገባ መወጣት እንዲችሉ፣ መንፈስ ቅዱስ እጅግ አስፈላጊ፣ «የሕይወት ኀይል» ነው::

የዐሥራ አንዱ ኀላፊነት ተልእኮአቸውን መወጣትና ለዚሁም የሚረዳቸው ልዩ የመንፈስ ቅዱስ ኀይል መቀበል ብቻ ሳይሆን ኀጢአትን ይቅር የማለት ሥልጣንም ይኖራቸዋል:: ይህ ማለት የቤተ ክርስቲያን ባለ ሥልጣናት የተለየ ሥርዐት በመፈጸም የሚያደርጉት የኀጢአት ስርየት አይደለም:: ጣትን ወደ ሰዎች በመጠቆም፣ «አንተ፣ ይቅር ተብለሃል ... አንተ፣ ይቅር አልተባልህም» የማለት ጉዳይም

[23] R.W. Lyon, "John 20:22, Once More," *ATJ* 43/1 (1988): 73-85 ላይ በውስጣቸው ከነበረው መንፈስ ቅዱስ የተነሣ ሐዋርያቱ በእርግጥ ክርስቲያኖች የሆኑት በዚህ ወቅት ነበር የሚለውን ጨምሮ የተለያየ የአተረጓጐም ሐሳቦችን ያቀርባል:: ይሁን እንጂ፣ የኋላ ኋላ፣ የሐዋርያት ሥራ 2÷4 በሉቃስ ወንጌል ውስጥ እንዳለው ስፍራ ሁሉ፣ ዮሐንስ 20÷22 በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ አለው ይላል:: ሁለቱም እንደሚናገሩት፣ የመንፈስ ቅዱስ መሰጠት ከአገልግሎት፣ ከኀይልና ሥልጣን ጋር ይያያዛል:: ኤም.ቢ. ተርነር ደግሞ ቀለል ያለና እጅግም አሳማኝ ያልሆነ አማራጭ አቅርቧል:: «መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ» የሚለው አንዴ ብቻ አለመሆኑንና ይልቁንም ሰዎች ለተለያየ ዓላማ በተለያየ ደረጃና ጊዜ እንደሚቀበሉ አመልክቷል ("The Concept of Receiving the Spirit in John's Gospel," *VE* 10 [1977]: 24-42) ምንም እንኳ ይህ ከብሉይ ኪዳን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ጋር የሚስማማ ቢሆንም፣ ሁኔታው በተለይ ከበዓለ ሃምሳ «ቅድመ ዕይታ» አኳያ ጥልቅ ፋይዳ ያለው ይመስላል::



አይደለም:: እዚህ ላይ ያለውን የኢየሱስን ንግግር ማቴዎስ 16÷19 እና 18÷18-20 ላይ ከተናገረው ጋር አብረን ማንበብ ይኖርብናል:: በዚያ ክፍል ቤተ ክርስቲያን በሁለት መንገዶች ኀጢአትን ይቅር ለማለት እንደምትችል እንመለከታለን:: የመጀመሪያው የሐዋርያቱ ስብከት ድነት የሚገኝበትን መንገድ ያመለክታል:: አስተምህሮአቸው ኢየሱስ ለቤተ ክርስቲያን ያለውን ፈቃድና ሥልጣን ያብራራል:: በሌላ አነጋገር ማን ውስጥ እንደ ሆነና ማን ውጭ እንደ ሆነ የሚወስነው የሐዋርያቱ ስብከት ይሆናል ማለት ነው:: በሁለተኛ ደረጃ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደ አካል ከቤተ ክርስቲያን ማገድን ጨምሮ የሥነ ሥርዓት ርምጃ የመውሰድ ሥልጣን አላቸው ማለት ይሆናል (ለምሳሌ 1ቆሮ 5):: ይህ አተረጓጐም ቍ 23 ውስጥ ያለውን ያልተለመደ ግሥ ምንነት ለመግለጽ ይችላል:: Perfect Verb ቢሆን ኖሮ «እናንተ ይቅር የምትሉት ኀጢአት ይቅር ተብሏል፤ እናንተ ይቅር ያላላችሁት ኀጢአት ይቅር አልተባለም» በሚል ሁኔታ[24] ይተረጐም ነበር:: ስለሆነም ይህ ክፍል ለደቀ መዛሙርቱ በተለይም ለዐሥራ አንዱ ሐዋርያት ሦስት ነገሮችን ያቀዳጃቸዋል:: (1) የመስበክ ተልእኮ አላቸው፤ (2) ስደት ይደርስባቸዋል፣ (3) ኢየሱስ በቤተ ክርስቲያን ያለው ሥልጣን ናቸው::

24በዚህ ጊዜ ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ የሆነው፣ ዲዲሞስ የተባለው ቶማስ፣ ኢየሱስ በመጣ ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አልነበረም:: 25ሌሎች ደቀ መዛሙርትም፣ ጌታን አየነው እኮ!» አሉት::

ዮሐ 20÷24-25

እርሱ ግን፣ «በምስማር የተቸነከረትን የእጆቹን ምልክቶች ካላየሁ፣ ምስማሮቹ በነበሩበት ቦታ ጣቴን ካላደረግሁ፣ በጐኑም እጄን ካላስገባሁ አላምንም አለ::

[24] Cf. J.R. Mantey, "Evidence That the Perfect Tense in John 20:23 and Matthew 16:19 is Mistranslated," *JETS* 16(1973): 129-138.

*መንትያው* ቶማስ (ዲዲሞስ) ምክንያቱ ግልጽ ባልሆነ ሁኔታ በዚያ ምሽት ስብሰባ ላይ አልነበረም:: ለሁለተኛ ጊዜ ኢየሱስን ካዩት በኋላ ስለ ሁኔታው ሊነግሩት ሳይሄዱ እንዳልቀሩ ግልጽ ነው:: አሁን ኢየሱስን እንዳዩት በመናገር ላይ ያሉት ጥቂት ቀባኂሪ ሴቶች ብቻ አይደሉም:: ጴጥሮስ፣ በኤማሁስ መንገድ ላይ የነበሩት ሁለቱ ሰዎችና ሌሎች ሐዋርያትም ይህንኑ ይመሰክራሉ:: ብዛት ያለው ማረጋገጫ አለ:: ቶማስ ላይ ከሚታዩት ሁለት ሌሎች የሕይወት ገጽታዎች የምንረዳው ከክርስቶስ ለመሞት ፈቃደኛ እስከ መሆን ድረስ የተሰጠ የክርስቶስ ተከታይ መሆኑን እንመለከታን (ዮሐ 11÷16 እና 14÷5):: የጨለምተኛነት ዝንባሌም ነበረው::

ኢየሱስ መሞቱን ያውቃል:: ምንም እንኳ ሳይንሳዊ አስተሳሰብ ባየለበት ዘመን ባይኖርም የሞቱ ሰዎች እንደማይራደሙና እንደማይነጋገሩ ያረዳል:: ትንሣኤውን በተመለከተ ግልብ አሳቢ ወይም ይሆናል ብሎ ጠባቂ አልነበረም:: ለማመን ማየትና የኢየሱስን ቁስሎች መዳሰስ ነበረበት::

**§ 179**
**ከዐሥራ አንዱ ጋር ለቶማስ መታየቱ**
**(ዮሐ 20÷26-31፤ 1ቆሮ 15÷5)**

[ዮሐ 20][26]ከስምንት ቀን በኋላም፣ ደቀ መዛሙርቱ በቤት ውስጥ ነበሩ፤ ቶማስም ከእነርሱ ጋር ነበር፤ በሮቹ ተቈልፈው ነበር፣ ኢየሱስ ግን መጥቶ በመካከላቸው ቆመና፣ «ሰላም ለእናንተ ይሁን» አላቸው:: [27]ከዚያም ቶማስን፣ «ጣትህን ወደዚህ አምጣ፤ እጆቼንም ተመልከት፤ እጅህን ዘርጋና በጐኔ አስገባ፤ አትጠራጠር እመን» አለው::

[28]ቶማስም፣ «ጌታዬ፤ አምላኬም!» አለው::

[29]ኢየሱስም፣ «አንተ ስላየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ ግን ብፁዓን ናቸው» አለው::



በቀጣዩ እሑድ ምሽት («ከስምንት ቀን በኋላ») ዐሥራ አንዱ እንደ ገና በአንድነት ነበሩ:: ቶማስም ከእነርሱ ጋር ነበር:: እንደ ቀድሞው በሩ ተዘግቶ ሳለ ነበር ኢየሱስ የታያቸው:: በዚህ ጊዜም፣ «ሰላም ለእናንተ ይሁን» በማለት ሰላምታ አቀረበ:: ከዚያም መገረም ተሞልቶ ወደ ነበረው ቶማስ ሄደ:: ቶማስ ሦስት ነገሮችን ፈልጎ ነበር፤ በምስማር የተቸነከሩ የአካሉን ክፍሎች ማየት፣ አንደኛውን ቍስሉን በጣቶቹ መንካት፣ በጦር የተወጋ ጐኑን መዳሰስ:: ምንም እንኳ ቶማስ ይህን ሲል እዚያ ባይኖርም (በአካል) ቶማስ የተናገረውን ሁሉ ኢየሱስ አውቋል:: ቶማስ በጠየቀው መሠረት ጣቶቹን በምስማር በተወጋ ቁስሉ፣ እጁን ደግሞ በጦር በቈሰለ ጐኑ ላይ እንዲያደርግ አዘዘው:: ቶማስ እንደታዘዘው ማደረጉን አናውቅም:: በ1ዮሐንስ 1÷1 መሠረት ግን ኢየሱስን አንድ ሰው የዳሰሰው መሆኑ ግልጽ ነው!

ተጠራጣሪነቱን እንዲተው ኢየሱስ ቶማስን አዘዘው:: እርሱም እንደ ታዘዘው አደረገ! ኢየሱስን በተመለከተ ከተነገሩት ታላላቅ ቃላት አንዱን ተናገሩ:: ለአንድ አይሁዳዊ ሌላውን ሰው፣ «ጌታዬና አምላኬ» ማለት ስድብ ነበር፡ ቶማስ ግን ገደቡን አልፎ ሄዷል፤ አሁን ኢየሱስ በሥጋ የተገለጠ አምላክ መሆኑን አምኗል::

«ተጠራጣሪው» ቶማስ በድንገት አማኝ ሆነ:: እርግጥ ነው ተጠራጣሪ ነበር:: እርግጥ ነው፣ ከማመኑ በፊት ተጨባጭ ማስረጃ ፈልጎ ነበር:: ሌሎቹም ቢሆኑ እንዲሁ አድርገዋል:: ያን ያደረጉት ቶማስ ያገኘውን ያህል ማረጋገጫ ባለማግኘታቸው ይሆናል:: የሌሎቹም ስሕተት የቶማስን የሚያህል ስሕተት ነበር:: ኢየሱስን እስኪያዩ ድረስ ለማመን አልፈለጉም:: ቶማስ ኢየሱስን በማየቱ አመነ:: ሳያዩ የሚያምኑ ግን እጅግ የበዛ በረከት ይጠብቃቸዋል:: ምስክርነቱ እውነት ነው:: ምስክሮቹ እምነት የሚጣልባቸው ናቸው:: አስተማማኝ በሆነ ምስክርነታቸው ብናምን ከኢየሱስ ምስጋናንና በስሙ ሕይወትን እንቀበላለን::

**ዮሐ 20÷30-31**

30ኢየሱስ በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፉ ሌሎች ብዙ
ታምራዊ ምልክቶችን በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ፤
31ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔር ልጅ
እንደ ሆነ እንድታምኑ፣ አምናችሁም በስሙ ሕይወት
እንዲኖራችሁ ይህ ተጽፎአል።

መጽሐፉ እዚህ ላይ ያበቃል። ዮሐንስ እንደሚለው፣ «ብዙ ማለት ይቻል ነበር፤ ብዙ መጻፍም ይቻል ነበር።» እንደሚታሰበው በመጀመሪያው መቶ ዓመት ማክተሚያ ላይ ዮሐንስ ይህን ወንጌል በጻፈ ጊዜ ጽሑፍ ላይ የዋሉ ወንጌሎች ብዙ ነበሩ። ይሁን እንጂ ሰዎች አንብበው እንዲያምኑ ዮሐንስ እነዚህን ጥቂት ታምራዊ ምልክቶችን[25] ጽፎአል። ሰዎች በኢየሱስ በማመን የዘላለም ሕይወት ይኖራቸዋል።

**§ 180**
**ዓሣ በማጥመድ ለነበሩ ሰባት ደዘ መዛሙርት መታየቱ**
**(ዮሐ 21÷1-25)**

ምዕራፍ 21 ያለ ቦታው የገባ ይመስላል። በመሠረቱ፣ ወንጌሉ ያበቃው ዮሐንስ የጻፈበትን ዓላማ በተናገረ ጊዜ ነበር (20÷30-31)። በተጨማሪ ይህ ምዕራፍ በዮሐንስ ዘንድ ያልተለመዱ አንዳንድ ነገሮችን፣ ማለት የቤተ ሰብ ስም ማንሣትን (ቍ 2) እና ቍጥር 24 ላይ «እኛ» በሚል ቃል መጠቀምን ይዟል። ይህም አንዳንዶች ይህን ምዕራፍ የጻፈው

[25] ዮሐንስ ሰባት የኢየሱስ ምልክቶችን ጽፎአል፤ (1) ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ መለወጡን፣ (2) የሹሙን ልጅ መፈወሱን፣ (3) በቤተ ሳይዳ መጠመቂያ ቦታ የነበረውን ሰውየ መፈወሱን፣ (4) 5000 ሰዎች መመገቡን፣ (5) በባሕር ላይ መራመዱን፣ (6) ዐይነ ስውሩን መፈወሱንና፣ (7) አልዓዛርን ከሞት ማስነሣቱን። በዚህ ላይ ቤተ መቅደሱን ማንጻቱን፣ በድል መግባቱን፣ በጣም ብዙ ዓሣዎች መያዙን መጨመር ይቻላል። ይሁን እንጂ እነዚህ ከሰባቱ፣ «ምልክቶች» በዓይነት የተለዩ ናቸው።



ዮሐንስ አይደለም በሚል ድምዳሜ እንዲደርሱ ምክንያት ሆኗል። ይሁን እንጂ ዮሐንስ 21 ከተቀረው የመጽሐፉ ክፍል የተለየ መሆኑን የሚያረጋግጥ ቅጂ ባለመኖሩና የዮሐንስ አጻጻፍ ስልት የሚንጸባረቅበት በመሆኑ የጻፈው ዮሐንስ ነው ወይም ቢያንስ እርሱ በነገረው መሠረት ሌላ ሰው ጽፎታል እንላለን።[26]

ይህ ምዕራፍ በመጀመሪያው መቶኛ ዓት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁነኛ ስፍራ ነበረው (1) ጴጥሮስ እንደ ገና መመለሱን፣ (2) ኢየሱስ በእርግጥ ገሊላ ውስጥ መታየቱንና፣ (3) ዮሐንስ አይሞትም የሚለው አስተሳሰብ የተሳሳተ መሆኑን (ቍ 23) ለማሳየት ያገለግላል።

**ዮሐ 21÷1-6**

1ከዚያም በኋላ ኢየሱስ በጥብርያዶስ ባሕር እንደ
ገና ለደቀ መዛሙርቱ ታየ፤ በዚህም ሁኔታ ተገለጠ፤
2ስምዖን ጴጥሮስ፣ ዲዲሞስ የተባለው ቶማስ፣ የቃና
ዘገሊላው ናትናኤል፣ የዘብዴዎስ ልጆችና ከደቀ መዛሙርቱ ሌሎች ሁለት አንድ ላይ
ነበሩ፤ 3ስምዖን ጴጥሮስም፣ «ዓሣ ላጠምድ መሄዴ ነው» አላቸው። እነርሱም፣ «እኛ
ም ከአንተ ጋር እንሄዳን» አሉት። ወጥተውም ወደ ጀልባዋ ገቡ፤ በዚያ ሌሊት ግን
ምንም አላጠመዱም።
4ሲነጋም፣ ኢየሱስ በባሕሩ ዳርቻ ቆመ፤ ደቀ መዛሙርቱ ግን ኢየሱስ
መሆኑን አላወቁም ነበር።
5እርሱም፣ «ልጆች ዓሣ አላችሁ» አላቸው።
እነርሱም የለንም አሉት።

[26] ማስረጃዎቹን ለማመዛዘን የሚረዳ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ለማግኘት የS.S. Smalley, "The Sign in John 21," *NTS* 20 (1974): 275-288 ይመለከቷል። ስሞሊ እንደሚለው ዮሐንስ 21 የጠቅላላውን መጽሐፍ ነገረ መለኮታዊ ፋይዳ አጥርጥር አድርጎ ማቅረብ ብቻ ሳይሆን፣ ሌሎቹ ሰባት ምልክቶችን በተመለከተ የተለመደውን ዑደት ይከተላል፤ ለምሳሌ ዐረፍተ ነገሩ፣ ምልክት፣ ምስክር።

6እርሱም፣ «መረባችሁን ከጀልባው በስተ ቀኝ
ጣሉ፤ ዓሣ ታገኛላችሁ አላቸው። እነርሱም በጣሉ ጊዜ
ከዓሣው ብዛት የተነሣ መረቡን መጐተት አቃታቸው።

የፋሲካ በዓል ካበቃ በኋላ በተነገራቸው መሠረት ሐዋርያት ወደ ገሊላ ተመለሱ። እዚያም ኢየሱስ እስኪገለጥላቸው ድረስ ቆዩ (ማቴ 28፥7፤ ማር 16፥7፤ ሉቃ 24፥6)። ጴጥሮስ ሥራ ፈትቶ ከመቀመጥ ይልቅ ዓሣ ለማጥመድ ወደ ገሊላ ባሕር ሄደ (ዮሐንስ ጥብርያዶስ ይለዋል)። ጴጥሮስ ኑሮውን በዚህ ሐይቅ ላይ በማድረግ ለዓመታት ኖሯል፣ ምናልባት አሁንም ወደ ቀድሞ መተዳደሪያው መመለስ እንዳለበት አስቦ ይሆናል (ዮሐ 16፥32 ጋር ያነ)። ዓሣ የማጥመዱ ሥራ ላለፈው ሁለት ዓመት ያህል በዘብዴዎስና በሁለት የቤተ ሰቡ አገልጋዮች ሲከናወን ነበር። ጴጥሮስ የለመደውን ጀልባ ይዞ ወደ ማጥመዱ ሄደ። ከእርሱ ጋር ስድስት ሰዎች መጥተው ነበር። የሁለቱ ስም አልተጠቀሰም። እነዚህ ሁለት ሰዎች እንደ ጴጥሮስና እንድርያስ ሁሉ ኑሯቸውን በዚህች ከቅፍርናሆም ውጪ በነበረች ቤተ ሳይዳ፣ የዓሣ ማጥመጃ ሰፈር አድርገው የነበሩ የጴጥሮስ ወንድም እንድርያስና ፊልጶስ ሊሆኑ ይችላሉ። ምናልባትም ጀልባው ላይ ከነበሩት ሰዎች ይልቅ፣ ጀልባው ላይ የነበሩት ሰዎች ቁጥር የበለጠ ፋይዳ ሊኖረው ይችላል።

ሌሊቱን ሙሉ ሲደክሙ ቢያድሩም አንድም ዓሣ አልያዙም። ፀሐይ መውጣት ስትጀምር አሰልቺውን የጀልባ ማጽዳት ሥራቸውን ለማከናወን ጀልባቸውን ወደ ባሕሩ ዳርቻ መውሰድ እንዳለባቸው አሰቡ። አንድ ሰው በባሕሩ ዳርቻ ቆሞ አዩ። በግምት አንድ መቶ ክንድ ከሚሆን ርቀት፣ «ወዳጆቼ፣ ዓሣ የላችሁም እንዴ?» በማለት ጠየቃቸው። ከማን ጋር ይነጋገር እንደ ነበር አላወቁም። መልሳቸው አጭርና ግልጽ ነው፣ «የለንም!» (ያልተሳካላቸው ዓሣ አጥማጆች



እንደሚሉት ዓይነት)። እንግዳው ሰው፣ «መረባችሁን ከጀልባው በስተ ቀኝ ብትጥሉ እኮ ብዙ ዓሣ ለመያዝ ትችላላችሁ» አላቸው። እንደ እውነቱ ከሆነ ይህ የማይመስል ሐሳብ ነበር! የዐሥራ አምስት ጫማ ርቀት ምን ልዩነት ያመጣል? ግን ለምን አናደርገውም? እንደ ታዘዙት መረባቸውን በሌላ አቅጣጫ ሲጥሉ ድንቅ ነገር ሆነ።

**ዮሐ 21፥7-14**

7ኢየሱስ ይወደው የነበረው ደቀ መዝሙርም፣
ጴጥሮስን፣ «ጌታ እኮ ነው!» አለው። ስምዖን ጴጥሮስ፣
«ጌታ እኮ ነው!» የሚለውን ቃል በሰማ ጊዜ፣
አውልቆት
የነበረውን መደረቢያ ልብስ ታጠቀና ዘሎ ወደ ባሕሩ ገባ። 8ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት
ግን ከባሕሩ ዳርቻ የራቁት ሁለት መቶ ክንድ ያህል ብቻ ስለ ነበር ዓሣ የሞላበትን
መረብ እየሳቡ በጀልባዋ መጡ። 9ወደ ምድርም በደረሱ ጊዜ፣ ዓሣ በላዩ የነበረበት
የከሰል ፍምና እንጀራ አዩ።
10ኢየሱስም፣ «አሁን ካጠመዳችሁት ዓሣ አስቲ አምጡ» አላቸው።
11ስለዚህ ስምዖን ጴጥሮስ ወደ ጀልባዋ ወጥቶ መረቡን ወደ ምድር
ጐተተው፤ መረቡንም መቶ አምሳ ሦስት ትልልቅ ዓሣ ሞልተውት ነበር፤ ይህን ያህል
ቢይዝም መረቡ አልተቀደደም። 12ኢየሱስም፣ «ኑ ቁርስ ብሉ» አላቸው። ጌታ እንደ
ሆነ ዐውቀው ስለ ነበር፣ ከደቀ መዛሙርቱ፣ «አንተ ማነህ?» ብሎ ለመጠየቅ የደፈረ
አልነበረም። 13ኢየሱስም መጥቶ እንጀራውን አንሥቶ ሰጣቸው። 14እንግዲህ ኢየሱስ
ከሙታን ከተነሣ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ ሲታይ ይህ ሦስተኛ ጊዜ ነው።

የሚያውቀውን በማስታወስ ዮሐንስ የመጀመሪያው ሰው ነበር። ከዚህ በፊትም እዚያው ነበር። እንዲያውም ደቀ መዝሙር የመሆን ጥሪ ለመጀመሪያ ጊዜ የደረሰው ያኔ ነበር። ተአምራዊ በሆነ ሁኔታ መጀመሪያ ዓሣ ባጠመዱ ጊዜ ኢየሱስ፣ «ተከተሉኝ፣ እኔም ሰዎችን የምታጠምዱ አደርጋችኋለሁ» አላቸው (ሉቃ 5፡1-11፤ § 41)። ያ እንግዳ ያለ ጥርጥር ኢየሱስ ነበር። ዮሐንስ፣ «ጌታ እኮ ነው!» ሲል

ትክክል እንደ ነበር ችኩሉ ጴጥሮስ ወዲያውኑ ነበር ያወቀው:: ዓሣ ሲያጠምድ የሚለብሰውን መደረቢያ በመጣል ወደ ባሕሩ ዘሎ ገባ (ብዙ ጊዜ ዓሣ አጥማጆች ለሥራ እንዲያመቻቸው ከወገባቸው በላይ ራቁታቸውን ይሆናሉ፤ ወደ ባሕሩ ዳርቻ ሲመጡ ግን እንዲያ መልበስ የተለመደ አልነበረም):: ጴጥሮስ አንድ መቶ ክንድ ያህሉን ርቀት እየዋኘ ወደ ባሕሩ ዳርቻ መጣ:: ጀልባይቱ ከኋላው ትከተል ነበር:: ከጀልባይቱ ኋላ ደግሞ ዓሣ የሞላበት መረብ ይጎተታል:: ተሸክሞ ጀልባ ላይ ለመጫን በጣም ከባደ ነበር::

በባሕሩ ዳርቻ ኢየሱስ በጥቂት የከሰል ፍም ላይ ትናንሽ ዓሣዎች [*opsarion*] ያበስል ነበር:: ከዳቦ ጋር ጥሩ ምግብ ይሆናሉ:: የራሳቸውን ዓሣዎች እሳቱ ላይ መጨመራቸው ወይም ምግቡን በሙሉ ያዘጋጀው ኢየሱስ መሆኑ አልተነገረንም::[27] ይሁን እንጂ ካጠመዱት ዓሣ እንዲያመጡ ታዝዘዋል:: ጴጥሮስ በሌሎች እየተረዳ መረቡ ውስጥ የነበረውን ዓሣ ወደ ባሕሩ ዳርቻ ጐተተው:: ዓሣዎቹን ሲቈጥሩ ጥቃቅኖቹን ወደ ባሕሩ መልሰው ከጣሉ በኋላ አንድ መቶ አምሳ ሦስት አገኙ::[28] ባልተለመደ ሁኔታ መረቡ አልተቀደደም ነበር::

[27] የdefinite article አለመኖር ኢየሱስ አንድ ትንሽ ዓሣና አንድ ትንሽ እንጀራ ብቻ እንደ ነበረው ሊያመለክት ይችላል::

[28] 153 የተለያዩ ምሳሌያዊ ትርጓሜዎች ቢሰጡትም፣ አንዱም እንኳ አሳማኝ አይደለም፤ (1) በገሊላ ባሕር 153 የዓሣ ዓይነቶች ነበሩ:: ይህም የተለያዩ የሰው ዘሮች እንደሚድኑ የሚያመለክተውን ማቴዎስ 13፥47-48ን ያመለክታል:: ይህ ግምት የመጣው ከኦፒያን ባገኘው መሠረት ከጀሮም ነበር:: ይሁን እንጂ፣ ጀሮም ኦፒያን ያቀረባቸውን ምድቦች በመቍጠር ረገድ ጠንቃቃ አልነበረም:: ከዚህም በላይ ኦፒያን የጻፈው 176-180 ሲሆን ዮሐንስ 153 ቍጥርን ለተጠቀመበት ሁኔታ አጥጋቢ ማብራሪያ ሊሆን አይችልም:: (2) በአጠቃላይ ከ1-17 ያሉ ድምር ውጤቶችን ይወክላል:: 17=10 ትእዛዞች እና 7 የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ወይም ደግሞ፣ "'One Hundred Fifty-Three Large Fish' (John 21:11): *HTR* 42 (1949): 273-275 በተሰኘ መጣጥፉ R. Grant እንደሚለው ዓሣዎቹ ሲጠመዱ ሰባት ደቀ መዛሙርት ነበሩ፤ ዐሥሩ መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉ ነበሩ (ዮሐ 20፥24):: ስለሆነም በዮሐንስ ራእይ 7፥4 መሠረት 144000 እግዚአብሔር የዋጃቸውን ሁሉ እንደሚወክል



በቍጥር 12 መሠረት የኢየሱስ የትንሣኤ አካል የተለየ ይመስላል (ማር 16፡12፤ ሉቃ 24፥16፤ ዮሐ 20፥14 ጋር ያነ):: ኢየሱስ መሆኑ ግን አያሳስትም:: ጌታ ራሱ መሆኑን በተግባሩ አውቀዋል:: ጥርጣሬ ቢኖራቸው እንኳ እንጀራውን ሲቈርስና ዓሣውን ሲያከፋፍል እጆቹን ለማየት ይችላሉ:: ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ስብስብ ሲገለጥ ይህ ለሦስተኛ ነበር (እንደ እውነቱ ከሆነ ኢየሱስ ሰባት ጊዜ ታይቷል፤ ሆኖም በግል ለማርያም፣ ለጴጥሮስ፣ ለሴቶቹና በኤማሁስ መንገድ ለነበሩ ሁለት ሰዎች መታየቱ እዚህ ላይ አልተጨመረም):: ለተቃዋሚዎቹ ሳይሆን ለወዳጆቹ መገለጡ ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ ነው (ሐሥ 10፥41 ጋር ያነ):: ከሞት ከተነሣ በኋላ አልዓዛርን ለመግደል ከሞከሩ፣ በኢየሱስ ላይ እንደዚያ የማያደርጉበት ምክንያት አይኖርም (ዮሐ 12፥10):: አብረሃም እንዳለው፣ «ሙሴንና

እዚህም ላይ 153 ይህንኑ ይወክል ይላል:: (3) ስምዖን ዮና የሚለው የጴጥሮስ ስም በዕብራይስጥ ቍጥር ስሌት 153 ነው:: (4) 153=100 (አሕዛብ) + 50 (አይሁድ) +3 (ሥላሴ):: (5) ፊስጋ የሚባለው ተራራ ስም በዕብራይስጥ 153 ቍጥር አለው:: ይህ ሙሴ ለእስራኤል ሰንበት እንዳደረገ ሁሉ (ዘኍ 11፥16-25፤ 27፥17 ጋር ያነ):: በዮሐንስ 21 መሠረት ኢየሱስም የአዲሲቱ እስራኤል መሪዎችን መሰናበቱን ያሳያል (O.T. Owens, "One Hundred and Fifty Three Fishes," *ExpT* 100 [1988]: 52-54 ጋር ያነ):: (6) በዕብራይስጥ፣ «የእግዚአብሔር ልጆች» የሚለው ቃል 153 ቍጥር አለው:: ስለሆነም ዮሐንስ 21 አዲሶቹ፣ «የእግዚአብሔር ልጆች» ያመለክታል (J.A. Romeo, "Gematria and John 21:11 - The Children of God," *JBL* 97/2 [1978]: 263-264):: (7) መረብ ውስጥ ያሉት 153 ዓሣዎችና ኢየሱስ እጅ ላይ ያለው አንድ ዓሣ 154 ይሆናሉ:: ይህ ደግሞ የጥንት ቤተ ክርስቲያን ለኢየሱስ ሰጥተውት ለነበረው አንድ «ቀን» ከሚለው ግሪክኛ ቃል ቍጥር ጋር ይስማማል (cf. K. Cardwell, "The Fish on the Fire; Jn 21:9" *ExpT* 102 [1990]: 12-14):: (8) 153 ጂኦሜትሪያዊ atbash ነው:: የዕብራይስጥ ፊደሎችን ቍጥር ዋጋ ብታገለባብጡ፣ ከዚያም 70፣ 3 እና 80 ብትወስዱ የምታገኙት፣ "I," "X" እና "Θ" የተሰኙትን የግሪክ ፊደሎች ይሆናል:: በግሪክኛ «ዓሣ» ለማለት መጀመሪያ የምናገኘው እነዚህን ሦስት ፊደሎች ሲሆን፣ ይህም የጥንት ክርስቲያኖች ምልክት ነበር:: ይህ ቃል ለጥንት ክርስቲያኖች «ኢየሱስ ክርስቶስ፣ አምላክ፣ ልጅ፣ አዳኝ» የሚለውን የሚወክል ነበር (cf. N.J. McEleney, "153 Great Fishes [John 21:11] - Geometrical Atbash" *Biblica* 58 [1977]: 411-417).

ነቢያትን የማይሰሙ ከሆነ፣ አንድ ሰው ከሙታን ቢነሣ እንኳ አያምኑም» (ሉቃ 16÷31)::

**ዮሐ 21÷15-19**

15በልተው ካበቁ በኋላ፣ ኢየሱስ ስምዖን
ጴጥሮስን፣ «የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፤ ከእነዚህ አብልጠህ
ትወደኛለህን?» አለው::
እርሱም፣ «አዎን ጌታ ሆይ እንደምወድህ አንተ ታውቃለህ» አለው::
ኢየሱስም፣ «ጠቦቶቼን መግብ» አለው::
16ኢየሱስም ለሁለተኛ ጊዜ፣ «የዮና ልጅ፣ ስምዖን ሆይ፤ በእውነት ትወደኛ
ለህን?» አለው::
እርሱም፣ «አዎን ጌታ ሆይ፤ እንደምወድህ አንተ ታውቃለህ» አለው::
ኢየሱስም፣ በጎቼን ጠብቅ» አለው::
17ሦስተኛም ጊዜ፣ «የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፤ ትወደኛለህን?» አለው::
ጴጥሮስም ሦስተኛ ጊዜ ኢየሱስ፣ «ትወደኛለህን» ብሎ ስለ ጠየቀው ዐዘነ፣
«ጌታ ሆይ፣ አንተ ሁሉን ታውቃለህ፤ እንደምወድህም ታውቃለህ» አለው::
ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ «በጎቼን መግብ:: 18እውነት እልሃለሁ፤ ወጣት
ሳለህ ልብስህን ራስህ ለብሰህ ወደ ፈለግህበት ትሄድ ነበር፤ ስትሸመግል ግን እጅህን
ትዘረጋለህ፤ ሌላም ሰው ልብስህን አስታጥቆህ ልትሄድ ወደማትፈልግበት
ይወስድሃል::» 19ኢየሱስ ይህን ያለው ጴጥሮስ በምን ዐይነት ሞት እግዚአብሔርን
እንደሚያከብረው ለማመልከት ነው:: ከዚህ በኋላም፣ «ተከተለኝ» አለው::

ወቅቱ ኢየሱስ ጴጥሮስን የሚገሥጽበትና የሚያስተካክልበት ነው:: ኢየሱስ ሦስት ጊዜ፣ «ትወደኛለህን? በማለት ጠየቀው፤ ጴጥሮስም ሦስተ ጊዜ፣ «አዎን፣ ጌታ ሆይ፣ እንደምወድህ ታውቃለህ» በማለት መለሰ:: ኢየሱስ ለሦስት ጊዜ፣ «በጎቼን መግብ» አለው:: ይህ በአማርኛው መሠረት ነው:: በግሪክኛው ግን አንዳንድ ረቀቅ ያሉ ተመሳሳይ ነገሮች ይኖራሉ:: ምናልባትም ጥበባዊ የአነጋገር ልዩነትን ያንጸባርቃሉ ለማለት ይቻላል:: ምናልባትም ጥልቅ ትርጓሜ



ይኖራቸው ይሆናል:: ውሳኔው የአንባቢው ነው:: የሚከተለው ሰንጠረዥ ረቀቅ ያሉ ለውጦችን ያሳያል::

| **የኢየሱስ ጥያቄ** | **ጴጥሮስ የሰጠው መልስ** | **የኢየሱስ አፀፋ** |
|---|---|---|
| ከእነዚህ አብልጠህ ትወደኛለህን? [*agapao*] | እንደምወድህ [*phileo*] ታውቃለህ [*oida*] | ጠቦቶቼን [*arnia*] መግብ [*bosko*] |
| ትወደኛለህን? [*agapao*] | እንደምወድህ [*phileo*] ታውቃለህ [*oida*] | በጎቼን [*probata*] ጠብቅ [*poimaino*] |
| ትወደኛለህን? [*phileo*] | እንደምወድህ [*phileo*] ታውቃለህ [*ginosko*] | በጎቼን [*probata*] መግብ [*bosko*] |

እዚህ ላይ አራት ተመሳሳይ ነገሮች እናያለን:

(ሀ) ፍቅር - የአዲስ ኪዳን መለኮታዊ ፍቅር [*agapao*]፣ ከውድ ጓደኛ ጋር ሲነጻጸር [*phileo*].[29]

[29] ይሁን እንጂ ዮሐንስ ወንጌል ውስጥ እነዚህ ሁለት ቃሎች ያለ ምንም ጉልህ ልዩነት እግዚአብሔርንና ሰውን በሚመለከት ሁኔታ ጥቅም ላይ ውለዋል (3÷16፤ 5÷20፤ 14÷21፤ 16÷27 ጋር ያነ):: ኢየሱስና ጴጥሮስ ይህን ሐሳብ በተለዋወጡ ጊዜ *agapao* የሚለው ቃል አሁን ያለው ነገረ መለኮታዊ አንድምታን ገና እንዳላገኘ ግልጽ መሆን አለበት:: ስለሆነም፣ «የምወድ ስለ ሆንሁ እወድሃለሁ» ከሚለው ይልቅ፣ «መወደድ ያለብህ ስለ ሆንህ እወድሃለሁ» ሲባል ጥቅም ላይ የሚውለው *phileo* ጥንካሬ ያለው ሊሆን ይችላል:: በሌላ በኩል ደግሞ ይህ የሐሳብ ልውውጥ የተደረገው በአራማይስጥ ቋንቋ ከሆነ፣ በ33 ዓ.ም. እነዚህ ቃላት ምንም ተጨማሪ ትርጉም አልነበራቸውም:: ስለሆነም ክርክሩ ዮሐንስ መጽሐፉን ሲጽፍ ዓላማው ምን እንደ ነበር በማሰቡ ላይ ይሆናል ማለት ነው:: በሁለቱም በኩል ያለውን የቋንቋ አጠቃቀም ጉዳይ ሰፋ ባለ ሁኔታ ለማየት R. Leedy, "Two Loves or One?" *BV* 34/1 (2000): 35-53 ይመ::

(ለ) ዕውቀት - አእምሮአዊ ዕውቀት [*oida*]፣ ከግላዊና የልምድ ዕውቀት ጋር ሲነጻጸር [*ginosko*].

(ሐ) መግብ/ተንከባከብ - መመገብ ብቻ [*bosko*] ከእረኛ ወይም ጠባቂ [*poimaino*] ጋር ሲነጻጸር

(መ) ጠቦት - ትንሽ በግ [*arnia*] ከትልቅ በግ [*probata*] ጋር ሲነጻጸር::

ተነጻጻሪ ነገሮች ጐን ለጐን መቀመጣቸው ተገቢ ይሆናል:: ይሁን እንጂ እነዚህ ተነጻጻሪ ነገሮች የተለያየ ትርጓሜ እንዳላቸው የሚያመለክት ምንም ዐውዳዊ ፍንጭ የለም:: ስለሆነም ከሚፈለገው በላይ የተለየ ፋይዳ እንዳንሰጠው ጥንቃቄ ማድገፍ አለብን:: ግልጽ ሆኖ የሚታየው ትርጓሜ ትኩረታችንን ለመሳብ በቂ ነው::

ከቁርስ በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስን በቀድሞ ስሙ፣ ሐዋርያ ከመሆኑ በፊት በነበረ ስሙ አናገረው:: አነጋገሩ ውስጠ ወይራ ያለበት ቢሆንም ምን ማለት እንደ ሆነ ጴጥሮስ በትክክል ተረድቷል:: ጥያቄው ቀላልም፣ የሚያሳምም ነበር፤ «ከእነዚህ አብልጠህ ትወደኛለህን?»

«እነዚህ» የሚለው ከዓሣ አጥማጅ ጓደኞቹ ተቃራኒ በሆነ መልኩ ሌሎች ደቀ መዛሙርትን የሚመለከት ሊሆን ይችላል:: ሐሙስ ምሽት ጴጥሮስ፣ «ሌሎች በሙሉ ቢክዱህም እኔ አልክድህም» (ማቴ 26÷33፤ ማር 14÷29) በማለት ተናግሮ ነበር:: ኢየሱስ ይህንኑ እንኳ ጋታውስ እያደረገው ነበር:: ጴጥሮስ ፋክራው ምን ያህል ሞኝነት እንደ ነበር ተረድቷል:: ቢሆንም ለጌታ ምን ያህል ጥልቅ ፍቅር እንዳለው ኢየሱስ ይገነዘባል:: ኢየሱስ ጥያቄውን ለሁለተኛና ለሦስተኛ ጊዜ ደጋግሞ ሲያቀርብ የጴጥሮስ ፍቅር ከሌሎች ደቀ መዛሙርት ጋር የማይወዳደር ስለ ነበረ ጴጥሮስ ክፉኛ ተሰምቶታል:: ቀላል በሆነ አቀራረብ «ትወደኛለህን?» በማለት ጠየቀው፤ ጴጥሮስም ይበልጥ ጠንከር ባለ መልኩ እንደ በፊቱ ያለ መልስ ሰጠ:: ቀጥሎ ከበፊቱ



ይልቅ ልብን ሰርስሮ በሚገባ ሁኔታ ለሦስተኛ ጊዜ ጠየቀው:: ምንም እንኳ የሚያመጣው ለውጥ ባይኖርም ኢየሱስ ጥያቄውን ከአጋፔ (*agapao*) ወደ ፊልዮ (*phileo*) በመለወጥ ላይ አልነበረም:: ደስ የማይለው ስሜት የመጣው ኢየሱስ ጴጥሮስን በአንድ ዓይነት ጥያቄ ሦስቴ ባፋጠጠው ጊዜ ነበር:: ድርጊቱ በፋሲካ ምሽት ጴጥሮስ ኢየሱስን ሦስት ጊዜ መካዱን የሚያሳስብ ነው::

ምንም እንኳ ይህ ጴጥሮስን የሚያስከፋው ቢሆንም፣ የኢየሱስ ቸርነት የታየበትም ነበር:: በእነዚያ ታዋቂ ሰዎች ፊት ጴጥሮስን መንጋውን ችላ በማለት ጥፋት ወቀሰው:: አዎን፣ ጴጥሮስ ኢየሱስን በጣም አሳዝኖአል:: ያ ማለት ግን ከእንግዲህ ዋጋ የሌለው ሰው ነው ማለት አይደለም:: የመንግሥተ ሰማይ መክፈቻዎች አይሰጡትም ማለትም አይደለም:: በስሕተቱ ከኢየሱስ ተገቢውን እርምት ተቀብሏል:: ከእንግዲህ ማንም ያን ማድረግ የለበትም::

በመጨረሻ ጴጥሮስ ሙሉ በሙሉ ሰዎችን በማጥመድ ሥራ ተሰማራ:: ከእንግዲህ እንደ ሰባኪ ረጅምና ፍሬያማ ተግባር ሊኖረው ነው:: ግንፍልነቱና የራስ ነጻነትን ወዳድ የሆነ ሕይወቱ (ጠንከር ባለ ሆኖም በክብር) ወደ ፍጻሜ በመቃረብ ላይ ነው:: ጴጥሮስ በመስቀል የሰማዕትነትን ሞት የሚሞት ስለ መሆኑ ኢየሱስ ትንቢት በመናገር ላይ ነው:: ትውፊት እንደሚለው ጴጥሮስ በ68 ዓ.ም. በኔሮ ዘመን ተሰቅሎአል:: ይሁን እንጂ እንደ ጌታው መሞት የማይገባው መሆኑን ገልጸ ዘቅዝቀው እንዲሰቀሉት ስለ ጠየቀ የጠየቀው ተደረገለት::

[20]ጴጥሮስም ወደ ኋላው ዞሮ ሲል፣ ኢየሱስ ይወደው የነበረ ደቀ መዝሙር ሲከተላቸው አየ፤ ይህም ደቀ መዝሙር ያን ጊዜ ራት ሲበሉ ወደ ኢየሱስ ደረት ተጠግቶ «ጌታ ሆይ፣ አሳልፎ የሚሰጥህ ማን ነው?» ያለው ነበር:: [21]ጴጥሮስም ባየው ጊዜ፣ «ጌታ ሆይ፣ እርሱስ?» ብሎ ጠየቀ::

**ዮሐ 21÷20-25**

[22]ኢየሱስም፣ «እስከመስስ ድረስ በሕይወት እንዲኖር ብፈልግ አንተን ምን ቸገረህ? አንተ ራስህ ተከተስኝ» አለው:: [23]በዚህ ምክንያት ይህ ደቀ መዝሙር አይሞትም የሚል ወሬ በወንድሞች መካከል ተሰራጨ:: ኢየሱስ ግን፣ እስከመስስ ድረስ በሕይወት እንዲኖር ብፈልግ አንተን ምን ቸገረህ?» አለው እንጂ እንደማይሞት አልነገረውም::

[24]ስለ እነዚህ የሚመሰክረውና ይህን የጻፈው ይኸው ደቀ መዝሙር ነው፤ ምስክርነቱም እውነት እንደ ሆነ እናውቃለን::

[25]ኢየሱስ ያደረጋቸው ሌሎችም ብዙ ነገሮች አሉ፤ ሁሉም ነገር ቢጻፍ፣ ለተጻፉት መጻሕፍት ሁሉ ዓለም በቂ ቦታ የሚኖረው አይመስለኝም::

ዮሐንስ ይከተላቸው ነበር:: ጴጥሮስ ዘወር ብሎ ካየው በኋላ የዮሐንስ ዕጣ ፈንታ ምን እንደሚሆን ጠየቀ:: በአጭር አነጋገር ኢየሱስ፣ «ይህ የአንተ ጉዳይ አይደለም:: ይልቁም የራስህን ድርሻ ተወጣ» ማለቱ ነበር:: የተናገረበት መንገድ ግን ዮሐንስ አይሞትም ለሚል ወሬ መነሻ ምክንያት ሆነ:: ትውፊት እንደሚለው የሰማዕትነት ሞት ያልሞተ ዮሐንስ ብቻ ነበር፤ ሆኖም ሞቷል:: ይህ ትንሽ ጭማሪ ቃል ሌላው ቀርቶ በዮሐንስ ዘመን እንኳ ያ ወሬ የተሳሳተ መሆኑን ሊያሳይ ይችል ነበር::

ስሙን ባይጠቅስም ዮሐንስ የመጽሐፉ ጸሐፊ መሆኑ ተመልክቷል:: የተወደደ ሐዋርያ ነበር:: በፋሲካ ራት በኢየሱስ አጠገብ ተቀምጦ የነበረና እንደማይሞት የተነገረለት ነበር:: የኢየሱስ አገልግሎት ጎዓይን ምስክር ነበር::[30] የኢየሱስን ቃልና ተግባር

[30] በቊ 24 ላይ «እኛ» የሚለው ከዮሐንስ አጻጻፍ ጋር የማይሄድ ነው:: መግለጫ ሊሆኑ ከሚችሉት በርካታ መንገዶች በአንዱ መንገድ ሊገለጽ ይችላል:: የመጀመሪያው «እኔ» ከማለት ጋር ሲነጻጸር በሚችል መልኩ በጥያቄ አቀራረብ «እኛ» የሚል ሊሆን ይችላል:: አለዚያም *oidamen* ማለትም «እናውቃለን» ለሁለት ተከፍሎ *oida men* «እኔ በእርግጥ አውቃለሁ» ማለትም ይሆናል:: ከዚህ በተረፈ የዮሐንስን ቃል ተቀብለው የሚጽፉ ሰዎች ሥራም ሊሆን ይችላል::



አስመልክቶ ስፍር ቍጥር የሌላቸው ቅጆችን ለመጻፍ ሲችል፣ እነዚህን ትናንሽ ነገሮች በመምረጥ በአጭሩ ገልጿቸዋል:: አንባቢው ኢየሱስን ወደ ማመን እንዲመጣ ለማድረግ ግን እነዚህም በቂ ናቸው::

**§ 181**
**ታላቁ ተልእኮ**
**በገሊላ**
**(ማቴ 28፥16-20፤**
**[ማር 16፥15-18])**

በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ታላቁ ተልእኮ እንደ ሐዋርያት ሥራ ሁሉ በአራቱም ወንጌሎች ተደጋግሞአል (ማቴ 28፥18-20፤ ማር 16፥16-18፤ ሉቃ 24፥45-49፤ ዮሐ 20፥21፤ ሐሥ 1፥8):: በአጭር ቃል እነዚህ ወደ ፊት እንድንገሠግሥ የሚያነሣሡ ትእዛዞች ናቸው:: ሥልጣን ሁሉ የኢየሱስ የመሆኑን ሐቅ መሠረት በማድረግ በማጥመቅና እርሱ ያዘዘውን እንዲጠብቁ በማስተማር ሕዝቦችን ሁሉ በወንጌል መድረስ ይኖርብናል:: ይህን ካደረግን ምንጊዜም ኢየሱስ ከእኛ ጋር ይሆናል::

**ማቴ 28፥16-17**

[16]ከዚያም ዐሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት በገሊላ ወደሚገኘውና ኢየሱስ ወዳመለከታቸው ተራራ ሄዱ:: [17]ባዩትም ጊዜ ሰገዱለት፤ ጥቂቶች ግን ተጠራጠሩ::

ደቀ መዛሙርት ኢየሱስ የሰጠውን መመሪያ በመታዘዝ ከፋሲካ በዓል በኋላ ወደ ገሊላ ሄዱ (ማቴ 28፥7:10):: እንዲህ ላለው ዓለም አቀፋዊ ተልእኮ፣ «የአሕዛብ ገሊላ» ትክክለኛ ቦታ ነበር:: መረዳት እንደሚቻለው ኢየሱስ ይህን የመሰሉ ስብሰባዎች ቀደም ሲልም አዘጋጅቶአል:: ብዙ ጊዜ እንደሚያደርገው የከበሩ እውነቶችን ለደቀ መዛሙርት ለማቅረብ ተራራውን እንደ መድረክ ተጠቅሞበታል (ማቴ 4፥8፤ 14፥23፤ 15፥29፤ 17፥1፤ 24፥3፤ 26፥30):: ኢየሱስን ሲያዩት የተደበላለቀ ምላሽ ነው የሰጡት፤ አንዳንዶች ሰገዱለት፤ ሌሎች ግን ተጠራጠሩ::

የተጠራጠሩ እነማን ነበሩ? «ሆይ፣ ዴ» (*Hoi de*) የሚለው ቃል ዐሥራ አንዱን፣ ከእነርሱ ጥቂቶቹን፣ ወይም ሌሎች ወገኖችን የሚመለከት ሊሆን ይችላል:: ይሁን እንጂ ቀደም ሲል በማቴዎስ ወንጌል ላይ ጥቅም ላይ ከዋለበት 25 ጊዜ አንጻር እዚህ ላይ የሚመለከተው ዐሥራ አንዱን ነው:: የሰገዱለትም ሆነ የተጠራጠሩት ሐዋርያት ነበሩ::

ማነው የተጠራጠረው? የምንነጋገረው ስለ ዐሥራ አንዱ ነው? ግማሾቹ ወይስ ፍጹም የተለየ ቡድን? ቀደም ሲል ማቴዎስ ውስጥ 25 ጊዜ እንደ ተጠቀመበት ግን የሚናገረው ስለ ዐሥራ አንዱ ሊሆን ይችላል:: ያመለኩትና የተጠራጠሩት ሐዋርያት ይመስላሉ:: የምንነጋገረው ስለ ዐሥራ አንዱ ከሆነ ለምን ተጠራጠሩ? «መጠራጠር» [*distazo*] የሚለው ቃል እምነታቸው ይወላውል ነበር ማለት እንጂ ማመን አልፈለጉም ማለት አይደለም:: ይህ ቃል ሌላ ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለው ማቴዎስ 14፥31 ውስጥ ብቻ ነበር:: ጴጥሮስ በባሕሩ ላይ ለመራመድ በሚሞክርበት ጊዜ የሰጠመ መሆኑን ነበር የሚገልጠው:: ጴጥሮስ እምነት እንደ ነበረው ግልጽ ቢሆንም ለዚያ ተግባር የሚያበቃው አልነበረም:: እነዚህን ቃሎች ማንበብ ያለብን ከዚህ አኳያ ነው:: እያመነቱ እንጂ ላለማመን እየተቃወሙ አልነበረም:: የሐዋርያቱን ምስክርነት በመቀበል ቢያምኑ የተሻለ ቢሆንም፣ ግትር ወይም እምቢተኛ ነበሩ ማለት አይደለም:: እዚህ ላይ ማቴዎስ ያሳየው ግልጽነት የሚገርም ነው:: ይህ እውነተኛ ታሪክ እንጂ ፈጠራ አለመሆኑን አሳየ::

**ማቴ 28፥18-20**

[18]ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱ ወዳሉበት ቀርቦ
እንዲህ አላቸው፤ «ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር
ተሰጥቶኛል፤ [19]ስለዚህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ በአብ፣
በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀ
መዛሙርቴ አድርጓቸው፤ [20]ያዘዝኋችሁንም ሁሉ
እንዲጠብቁ አስተምሯቸው፤ እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ
ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ::»



ኢየሱስ በሚያወላውሉ ደቀ መዛሙርት ፊት ነገሩን በትክክል በማስቀመጥ ላይ ነበር:: እርሱ ከሁሉም በላይ ነው:: ስለ ሥልጣኑ ደጋግሞ ተናግሯል (ማቴ 9፥6:8፤ ሉቃ 9፥1፤ 10፥19፤ ዮሐ 5፥27፤ 10፥18፤ 17፥2)፣ ትንሣኤውም ያን አረጋግጧል:: እርሱ በሥጋ የተገለጠ እግዚአብሔር ነው፤ እንደ እግዚአብሔርነቱም በሰማይና በምድር ይገዛል:: እርግጥ ለአባቱ መገዛቱን ይቀጥላል፤ ይኸው ብቻ ነው (1ቆሮ 15፥27-28)::

የኢየሱስን ሥልጣን መሠረት በማድረግ ሕዝቦችን ሁሉ ደቀ መዛሙርት ማድረግ ይኖርብናል:: ቍጥር 19 አንድ ዋነኛ ግሥና ሦስት ደጋፊ የግሥ ዓይነቶች አሉት:: ዋነኛው ግሥ፤ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው! የሚለው ነው:: ሌሎቹ ግሦች ያን እኛ እንዴት እንደምናደርገው ይገልጻሉ:: መጀመሪያ መሄድ አለብን:: እዚህ ላይ «ሂዱ» የሚለው ግሥ፣ «ስትሄዱ ደቀ መዛሙርት አድርጉ» በሚል መልኩ ሊቀመጥ ይችላል:: ይህን መሠረት በማድረግ አንዳንዶች ተልእኮው በምንሄድበት ሁሉ ደቀ መዛሙርት ማድረግ እንዳለብን ብቻ ነው የሚያመለክተው ብለዋል::[31] ኢየሱስ ያለው ግን ይህን ነበር ለማለት አይቻልም:: በሥነ ልሳን ደረጃ መደረግ ያለበት ዋና ግሥ ጠንከር ያለ መልእክት «ይዟል::»[32] በሌላ አነጋገር እንድንሄድ ታዝዘናል:: ከዚያም በላይ ዐውዱ ለዚህ አጽንዖት የሚሰጥ ይመስላል:: ወንጌልን ለማዳረስ በዓላማ ድንበሮችን ተሻግረን ካልሄድን ሕዝቦችን እንዴት ደቀ መዛሙርት ለማድረግ ይቻላል? ኢየሱስ የሚያዘው፣ ዓለምን ሁሉ የሚያዳርስ ሚሲዮናዊ እንቅስቃሴ እንዲደረግ

---

[31] E.g. R. Duncan Culver, "What is the Church's Commission? Some Exegetical Issues in Matthew 28:16-20," *BETS* 10 (1967): 115-126.

[32] ይህን አወቃቀርን በተመለከተ ሌሎች ምሳሌዎች 2፥13:20፤ 5፥24፤ 11፥4፤ 21፥2 ይመለከቷል:: ከC. Roger's, "The Great Commission," *BibSac* 130 (1973): 258-267 ጋር ያነ::

ነው:: እዚህም ላይ ግን ሚስዮናዊ ሥራን ባለንበት ቦታ ወንጌልን ከማዳረስ በላይ በማግዘፍ በአገርና በውጭ አገር ሚስዮናዊ እንቅስቃሴ መካከል ያለውን ልዩነት በተመለከተ የቅዱሳት መጻሕፍት ድጋፍ በሌለው ድምዳሜ ላይ እንዳንደርስ መጠንቀቅ አለብን:: ኢየሱስ ሁለቱንም አዟል:: እርሱ የሰጠንን ተግባር ለመፈጸም ሁለቱም አስፈላጊዎች ናቸው:: ቍጥር 19 ውስጥ ያሉት ሁለተኛውና ሦስተኛው የግሥ ዓይነቶች፣ «ማጥመቅ» እና «ማስተማርን» የሚመለከቱ ናቸው:: በአንድነት ሲሆኑ ደቀ መዛሙርት የማድረግ ሂደትን ያመለክታሉ:: እነዚህ ነገሮች በአማኙ መንፈሳዊ ጉዞ የመለወጥና የዕድገት ምልክቶች ናቸው::

«በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም» የማጥመቅ (formula) ቀመርን አስመልክቶ ብዙ ተሠርቷል:: ይህ ጥቅስ ሥላሴን በተመለከተ ከፍተኛ ድጋፍ ሊሆነን ይችላል:: ይሁን እንጂ፣ በወንጌሎቹም ሆነ በመልእክቱ የምንመለከታቸው ሰዎች በሦስቱም ሳይሆን በኢየሱስ ስም ሲጠመቁ ነው:: ይህም ለተለያዩ ልምምዶች ምክንያት ሆኗል:: ለምሳሌ አንዳንዶች ሰው መጠመቅ ያለበት በኢየሱስ ስም ብቻ ነው ሲሉ፣ ሌሎች ደግሞ በእያንዳንዱ የሥላሴ አካል ስም በሦስት የተለያየ ጊዜ መጠመቅ እንዳለበት ይናገራሉ::[33] እንዲህ ያለው አክራሪነት በሁለት ምክንያቶች አቅጣጫ ስቷል:: በመጀመሪያ፣ እዚህ ላይ ኢየሱስ ልንከተለው የሚገባ፣ «ቀመር» (formula) ይሰጠናል ብለን ለማመን ምክንያት የለንም:: አስፈላጊው ጉዳይ አንድን ሰው ስናጠምቅ የምንናገራቸው ቃላት አይደሉም:: ዋና ነገር ሰዎች በኢየሱስ አዳኝነትና ጌትነት ማመናቸው፣ ለራሳቸው መሞታቸውና ከክርስቶስ ጋር መነሣታቸው ነው:: ሁለተኛ በኢየሱስ ስም መጠመቅ የተለያዩ ነገሮችን

[33] E.g., D.R. Plaster, "Baptism by Triune Immersion," *GTJ* 6/2 (1985): 383-390.



ተግባር ላይ ከማዋል ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም:: የኢየሱስ፣ «ስም» ሥልጣኑን፣ ዓላማውንና ባሕርዩን ይወክላል:: ስለሆነም ጥምቀት ውጤታማ የሚሆነው ሥርዓቱ ሲፈጸም በምናነበንባቸው አስማታዊ ድግምቶች አይደለም:: ጥምቀት «የሚሠራው» እኛን ከኀጢአት ለማንጻትና ወደ መንግሥቱ ለማምጣት ኢየሱስ ካለው ኀይልና ሥልጣን የተነሣ ብቻ ነው (1ጴጥ 3፥21፤ ሐሥ 2፥38):: ስንጸልይም ተመሳሳይ ስሕተት እንፈጽማለን፤ «በኢየሱስ ስም አሜን» በማለታችን ብቻ በኢየሱስ ስም እንደ ጸለይን እናስባለን:: በቃላት ቀመር እየጸለየ ወይም በኢየሱስ ስም እየተጠመቀ ላለ ሰው የሚኖረው ጠቀሜታ በጣም ትንሽ ነው::

ጥምቀት በሂደት ላይ ያለ ለውጥን እንደሚያሳይ ሁሉ፣ ትምህርትም የክርስቲያንን ዕድገት ያቀላጥፋል:: ይህ የዕድሜ ዘመን ሂደት ነው:: ይሁን እንጂ ቢያንስ የሚከተሉትን ለማለት ይቻላል፤ (1) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሙሉውን የእግዚአብሔር ሐሳብ መስበክ አለባቸው:: ቤተ ክርስቲያን በመፈሳዊነት እንድታድግ ከተፈለገ ነገረ መለኮትንና አስቸጋሪ የሚመስሉየቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶችን በጥልቀት መመርመር ይኖርብናል:: (2) ክርስቲያናዊ ትምህርት የቤተ ክርስቲያን ዋና ተግባር ነው:: በስብከት፣ በእሑድ ትምህርት ቤት፣ በቤት ለቤት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ በቴሌቪዥን ወይም በሬዲዮ ሊሆን ይችላል፤ ክርስቲያናዊ ትምህርት ዋነኛው የቤተ ክርስቲያን ዓላማ ሊሆን ይገባል:: ኢየሱስ ሰዎች ስለ እርሱ እንዲማሩ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንድናመጣቸው ተልዕኮ አልሰጠንም:: ይህን መልእክት ለዓለም ማድረስ አለብን:: ክርስቲያኖች የሚሰበሰቡት በትምህርት ለመታነጽ ነው:: (3) ክርስቲያናዊ ትምህርት ወደ ትምህርት ተቋማት በመሄድ ብቻ መሆን የለበትም:: ግባችን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ማወቅ ሳይሆን፣ ይበልጥ ኢየሱስ ክርስቶስን መምሰል ነው:: ተግባር ላይ ካዋልነው የበለጠ እናውቃለን:: ብዙ ማወቃችን ይበልጥ ለክርስቶስ

እንድንኖር አለማድረጉ በጣም የሚገርም ነው:: ስለሆነም ክርስቲያናዊ ትምህርት የተማርነውን በተግባር በማዋሉ ላይ ማተኰር ይኖርበታል:: ተግባራዊና በእውኑ ሕይወት የሚታይ መሆን አለበት::

ማቴዎስ አሁን ታሪኩን ወደ ማጠቃለል መጥቷል:: የተሰጠን ትእዛዝ ሳይሆን ኢየሱስ ለሰጠው ተስፋ አጽንዖት በመስጠት ነው የሚደመድመው:: የአማኑኤል፣ «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር» (ማቴ 1፥23) የመሆኑ ተስፋ ፍጻሜም ይኸው ነው:: በመንፈስ ቅዱስ በኩል እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእኛ ጋር ይሆናል:: ከዚያ በኋላ ግን እንዴት የከበረ ሀሳብ ነው፤ ፊት ለፊት!

16የሚያምን የተጠመቀ ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል:: 17የሚያምኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ልሳንም ይናገራሉ፤ 18እባቦችን በእጃቸው ይይዛሉ፤ የሚገድል መርዝ ቢጠጡ እንኳ አይጐዳቸውም፤ እጃቸውንም በሕመምተኞች ላይ ይጭናሉ፤ እነርሱም ይፈወሳሉ::

*ማር 16፥16-18*

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው (§ 173) የማርቆስ ወንጌል መደምደሚያ ዐውዳዊ ችግሮች ይበዙበታል:: ከእነዚህ ዐውሳዊ ችግሮችም አልፎ ያልተለመደ አባባል ነው:: ቍጥር 16 በውሃ ውስጥ ጠልቆ የመጠመቅን በሚመለከት ማርቆስ ያቀረበውን ታላቅ ተልእኮ ይዟል:: ከዚያም (ሐዋርያትን ብቻ ሳይሆን) አማኞችን ሁሉ ስለሚከተሉ ተአምራዊ ምልክቶች ይዘረዝራል:: አጋንንትን ማስወጣታቸው አዲስ ነገር አይደለም:: በኢየሱስ አገልግሎት ዐሥራ ሁለቱም ሆኑ ሰባዎቹ ይህን አድርገው ነበር (ማር 6፥13፤ ሉቃ 10፥17):: ከሐዋርያት ሥራ እንደምንመለከተው ጳውሎስም እንዲህ አድርጓል (ሐሥ 16፥18):: እንዲያውም የኢየሱስ ስም በአጋንንት ላይ



ያለው ኀይል በኤፌሶን በጣም ታውቆ ነበር (ሐሥ 19፥13):: በልሳኖች መናገራቸው አይገርመንም:: ይህ ሁኔታ ሐዋርያቱን (ሐሥ 2፥1-4)፣ የቆርኔሌዎስ ቤተ ሰብን (ሐሥ 10፥44-48)፣ በኤፌሶን የነበሩ ዐሥራ ሁለት ደቀ መዛሙርትን (ሐሥ 19፥1-4) እንዲሁም የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያንን ነክቷል (1ቆሮ 14):: እርግጥ ነው በኢየሱስ ስም ተአምራዊ ፈውስ እንደሚኖር መጠበቅ አለብን:: ፈውስ ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አንዱ ነው (1ቆሮ 12፥9)::

የግድ መጠበቅ የሌለብን እባቦች መያዝንና መርዝ መጠጣትን ነው:: እንግዳና አዲስ ነገር ነው:: ደቀ መዛሙርቱ እባብና ጊንጥን (ሉቃ 10፥19 ስለ አጋንንታዊ ኀይላት ለማመልከት) እንደሚረግጡ ኢየሱስ ቀደም ሲል ተናግሮ ነበር:: መላጥያ ደሴት ላይ ጳውሎስን እባብ ቢነድፈውም አልጐዳውም (ሐሥ 28፥3-6):: አደገኛ መርዝ ስለ መጠጣት በቅዱሳት መጻሕፍት ምሳሌ የሚሆነን ሰው ባይኖርም፣ ይህን ጉዳይ በኀይለኛ እባብ ቢነደፉም ባልሞቱ ሰዎች ምድብ ውስጥ እናደርገዋለን:: እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ለማየት ለአፍታ እንኳ ለመታገሥ ከቻልን ይህ ጥቅስ መጀመሪያ ላይ የመሰለንን ያህል እንግዳና ያልተለመደ አይሆንብንም:: እባቦችን፣ መያዝና አደገኛ መርዝ መጠጣት እግዚአብሔርንም ሆነ ዕጣ ፈንታን መፈታተን ሊሆን አይችልም:: በመሠረታዊ ደረጃ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ክስተትና ልዕለ ፈተጥሮአዊ ጥበቃ ክርስቲያኖችን እንደሚከተላቸው የሚያሳይ ነው::

ይህ ጥቅስ አስገራሚ ነገሮች በሚታዩበት ቦታ ሳይሆን፣ የማርቆስ ወንጌል አንባቢዎች ሞትን በሚጋፈጡበት የሮማውያን አደባባይ ላይ መተግበር ነበረበት:: ምክንያቱም ስለ ክርስቶስ የሚመሰክሩ ክርስቲያኖች ከባድ ተቃውሞ ይገጥማቸው ነበር:: አንዳንዶም ከባድ መርዝ እንዲጠጡ በማስገደድ፣ አንዳንዶም ከአደገኛ የዱር አራዊት ጋር እንዲታገሉ በማድረግ የሞት ቅጣት

ይፈጸምባቸዋል:: ዝርዝሩ ይለያያል:: እባቦችን በአንበሶች ወይም ለማዳ ያልሆኑ ወሾች መተካት ይቻላል:: መርዙን በሰይፍ ወይም በመስቀል መተካት ይቻላል:: የሚጠበቀው ግን አንድ ነገር ነው፤ ሕዝቡን የሚወደውን ልዕል እግዚአብሔር እስካገለገላችሁ ድረስ በሕዝቡ መካከል ሲገኝ አንዳንድ አስደናቂ ነገሮችን እንደሚደርግ መጠበቅ ትችላላችሁ::

ይህ ጥቅስ ማንኛውም ክርስቲያን፣ ሌላው ቀርቶ አማኞች በአንድነት በሚሆኑበት ጊዜ እንኳን ተአምራዊ ምልክቶችን እንደሚያሳዩ አይናገርም:: ይልቁንም ቤተ ክርስቲያን ለእግዚአብሔር ስትቆም፣ እርሱም ከቤተ ክርስቲያኑ ጋር የሚቆም መሆኑን ነው የሚናገረው:: በመሠረቱ ማርቆስ 16፥17-18 እንደ ማቴዎስ 28፥20 (እና ሐሥ 1፥8) ታላቁን ተልእኮ በመፈጸም ረገድ የራሱ ድርሻ ይኖረዋል:: እግዚአብሔር በመካከላችን እንደሚሆን የሚያመለክት ተስፋ ነው:: ስለሆነም ወንጌልን ለተቃዋሚዎች ለማድረስ በሚያደርጉት ሙከራ ከባድ ነገር ለሚገጥማቸው አማኞች ይህ ጥቅስ መጽናኛ ሊሆናቸው ይችላል:: ማቴዎስ እንደሚለው እኛ ለዓለም ወንጌል ስንሰብክ፣ ኢየሱስ ከእኛ ጋር ይሆናል (ማቴ 28፥20):: ሉቃስ እንደሚለው እኛ ለዓለም ወንጌል ስንሰብክ መንፈስ ቅዱስ ኀይል ይሰጠናል (ሐሥ 1፥8):: ማርቆስ ደግሞ ለዓለም ወንጌል ስንሰብክ እግዚአብሔር ይጠብቀናል ይላል::

**§ 182**
**ለያዕቆብና ለአምስት መቶ ሰዎች መታየቱ**
**(1ቆሮ 15፥6-7)**

6 ከዚያም በኋላ ከአምስት መቶ በላይ ለሚሆኑ
ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ፤ ከእነዚህም አብዛኞቹ
በሕይወት አሉ፤ አንዳንዶቹ ግን አንቀላፍተዋል::
7 ከዚያም ለያዕቆብ ታየ፤ በኋላም ለሐዋርያት በሙሉ
ታየ::



አንድ ደረጃ ላይ ኢየሱስ ለወንድሙ ለያዕቆብና ከአምስት መቶ በላይ ለሆኑ ወንድሞች ታይቷል:: ጽሑፉ በሚያቀርበው መሠረት ኢየሱስ መጀመሪያ ለአምስት መቶዎቹ፣ ከዚያ በኋላ ለያዕቆብና ለሌሎች ሐዋርያት ነበር የታየው:: ይህ ኢየሱስ የታየበትን ጊዜ በመዘርዘር ረገድ ትክክል አይደለም:: ቅደም ተከተላዊ ይዘቱንም የጠበቀ አይሆንም:: በዚህ ክፍል መሠረት ኢየሱስ እሑድ ማታ ለሐዋርያቱ ከመታየቱ በፊት እሑድ ከሰዓት በኋላ ለያዕቆብና ለአምስት መቶዎቹ የታየ ይመስላል:: የዚህ ተቃራኒ አቀማመጥ ሐዋርያት፣ ከዚያ ያዕቆብ፣ ከዚያ አምስት መቶዎቹ የሚለው ነው::

እነዚህ ሁኔታዎች የተፈጸሙበት ትክክለኛ ጊዜ ግልጽ ባይሆንም፣ የትንሣኤን እውነታ አስመልክቶ ታላላቅ ማረጋገጫዎች ይሰጡናል:: መጀመሪያ፣ ያዕቆብ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪ ሆኗል (ሐሥ 12፥17፤ 15፥13፤ 21፥18፤ ገላ 2፥9) አዲስ ኪዳን ውስጥ በስሙ የሚጠራውን መልእክት የጻፈውም እርሱ መሆኑ ይታሰባል:: ሆኖም፣ ሁሌም ለኢየሱስ የቀረበ አልነበረም:: እንደሚታወቀው ኢየሱስ መስቀል ላይ በነበረ ጊዜ በሕይወት ያሉ ወንድሞች ያልነበሩት ይመስል ማርያምን አደራ የሰጠው ለዮሐንስ ነበር:: ይህ ከመሆኑ ስድስት ወሮች በፊት ያዕቆብን ጨምሮ ወንድሞቹ ማንነቱን ይገልጥ ዘንድ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲወጣ አጥብቀው ሲጠይቁት ነበር (ዮሐ 7፥1-5):: ኢየሱስ አእምሮውን እንደ ሳተ አድርገው በማሰባቸው፣ ይዘው ወደ ቤት ሊወስዱት ፈልገው ነበር (ማር 3፥31-32):: ከተጠራጣሪነት የቤተ ክርስቲያን ዐምድ ወደ መሆን ያዕቆብን የለወጠው ምን ነበር? ከትንሣኤው በቀር ሌላ አይደለም::

ከዚህም በላይ በአንድ ጊዜ አምስት መቶ የሚሆኑ ሰዎች አይተውታል:: ይህ የቁም ቅዠት አይደለም:: በጣም ብዙ ምስክሮች አሉ:: በተጨማሪም 1ኛ ቆሮንቶስ በሚጻፍበት ጊዜ ብዙዎች በሕይወት

እንደ ነበሩ ጳውሎስ ይናገራል (55 ዓ.ም.):: የፈጠራ ወሬ አልነበረም ማለት ነው:: እዚያ የነበሩ ሰዎችን ለማነጋገር ይቻል ነበር::

**§ 183**
**በኢየሩሳሌም ለሐዋርያት መታየቱ**
**(ሉቃ 24÷44-49፤ ሐሥ 1÷3-8)**

አንድ ዓይነት ሁኔታዎች የሆኑ ይመስል ሉቃስ 24÷44-49 ከየሐዋያት ሥራ 1÷3-8 ጋር አያይዘናቸዋል:: ሉቃስ የሚቀርበው ታሪክ የሚጀምረው ግን በትንሣኤው እሑድ ቍ 36 መሆኑን ልብ በሉ:: የሐዋርያት ሥራ ታሪክ የጀመረው በአርባዎቹ ቀኖች ማለቂያ ላይ ይመስላል:: የሁለቱም ታሪኮች ጸሐፊ የሆነው ሉቃስ ሁለቱንም መጻሕፍት ወደ አንድነት በሚያመጣ የአጻጻፍ ስልት ተጠቅሟል:: ነገሩ አንድ ፊልም ማብቂያ ላይ ከተከታዩ ፊልም ታሪክ ቀንጭቦ እንደሚቀርብና ፊልሙ መጀመሪያ ላይ ቀደም ሲል የነበረውን ፊልም ትውስታ የማስጨበጥ ያህል ይመስላል:: እዚህ ላይ የምንመለከተው አንድ ታሪክ ሳይሆን፣ በተለያየ ጊዜ የታዩትን ታሪኮች በአንድ ላይ ነው:: ሉቃስ በአርባዎቹ ቀኖች ኢየሱስ የታየባቸውን ታሪኮች በአጭሩ ለመናገር በሚያስችል መልኩ እጥር አድርጐ ማቅረቡ ነው:: የእርሱ ታሪክ በትንሣኤው እሑድ ላይ ያበቃና አርባዎቹን ቀኖች አሻግሮ ያያቸዋል፤ የሐዋርያት ሥራ መጀመሪያ ክፍል ግን በዕርገቱ ቀን ላይ ያቆምና አርባዎቹ ቀኖችን ወደ ኋላ ዘወር በማለት ይመለከታቸዋል::

*ሐሥ 1÷3*

[3]ከሕማማቱም በኋላ ራሱ ቀርቦ ሕያው መሆኑን፣ ለእነዚሁ በብዙ ማስረጃ እያረጋገጠላቸው አርባ ቀንም ዐልፎ ዐልፎ እየታያቸው ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ነገራቸው::



(ከእነርሱ ጋር በማእድ ተቀምጦ[ሐ/ሥ]) [44]እርሱ፣ «ከእናንተ ጋር በነበርሁ ጊዜ፣ በሙሴ ሕግ፣ በነቢያትና በመዝሙር መጻሕፍት ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው» አላቸው::

*ሉቃ 24÷44-48*
*ሐሥ 1÷4 ጋር*

[45]በዚህ ጊዜ ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዲያስተውሉ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው፤ [46]እንዲህም አላቸው፤ «እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፤ ክርስቶስ መከራን ይቀበላል፤ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል፤ [47]ከኢየሩሳሌም ጀምሮ ለሕዝቦች ሁሉ ንስሐና የኀጢአት ስርየት በስሙ ይሰበካል፤ [48]እናንተም ለዚህ ምስክሮቼ ናችሁ::

ኢየሱስ መጀመሪያ የታየው ከትንሣኤው በኋላ ባለው እሑድ ነበር:: ለመጨረሻ የታየው ከአርባ ቀን በኋላ ደብረ ዘይት ውስጥ ነበር:: አሁን ደግሞ ከትንሣኤው ሃምሳ ቀን በኋላ እሑድ ዕለት በዓለ ሃምሳ ተጀምሮአል:: ስለሆነም ኢየሱስ ወደ ሰማይ ያረገው ከዚህ በዓል አሥር ቀን አስቀድሞ ነበር ማለት ነው::

በአርባዎቹ ቀኖች ሕያው መሆኑን በተለያየ መንገድ አሳያቸው:: ሉቃስ ይህን፣ «በብዙ ማስረጃ» ይለዋል [*tekmerion*, ሐሥ 1÷3]:: አርስቶትል፣ «አሳማኝ ማስረጃ» ለማለት የተጠቀመው በዚህ ቃል ነበር (*Rhetoric* I. 2. 16):: ከእነርሱ ጋር ተነጋገረ፤ ከእነርሱ ጋር በላ፤ ለእነርሱ ታየ፤ ቁስሎቹን እንዲነኩ ፈቀደላቸው፤ እርሱ ብቻ ማስተማር በሚችለው ዓይነት አስተማራቸው:: ይህንኑ ዮሐንስ፣ «ከመጀመሪያው የነበረውን፣ የሰማነውን፣ በዐይኖቻችን ያየነውን፣ የተመለከትነውንና እጆቻችን የዳሰሱትን እንናገራለን - ሕይወት ተገለጠ፤ እኛም አይተነዋል» በማለት ገልጾታል (1ዮሐ 1÷1)::


በእነዚያ አርባ ቀኖች ኢየሱስ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ለደቀ መዛሙርቱ የሚያስተምራቸው ብዙ ነገር ነበረው (ሐሥ 1÷3)::

ከትንሣኤው በኋላ ያስተማራቸውን ዝርዝሮች ስናይ፣ በተለይ ስለ ሦስት ነገሮች ማስተማሩ ግልጽ ነው:-

1. መሲሓዊ ትንቢቶችን አብራራ (ሉቃ 24÷26-27:44-45፤ ሐሥ 1÷5)::



2. ዓለምን በወንጌል ስለ መድረስ ተናገረ (ማቴ 28÷18-20፤ ማር 16÷15-16፤ ሉቃ 24÷47-49፤ ዮሐ 20÷21)::
3. ሁልጊዜ (ማቴ 28÷20፤ ማር 16÷17-18) በተለይም ተአምራዊ ነገሮችን በማድረግ ከቤተ ክርስቲያን ጋር እንደሚሆን ተናገረ (ማር 16÷17-18፤ ሉቃ 24÷49፤ ሐሥ 1÷4)::



በአንድ ወቅት ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር ሲበላ ሳለ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ ነበራቸው:: ኢየሱስ ያስተማራቸው የብሉይ ኪዳንን ይዘት ብቻ ሳይሆን፣ እንዴት በተገቢ መልኩ እንደሚተረጐሙት ጭምር ነበር:: ከዚህ ምንባብ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጐም በዚያንስ ሦስት ነገሮችን እንማራለን:: በመጀመሪያ ክርስቶስን ማዕከል (Christocentric) ማድረግ አለበት:: ብሉይ ኪዳን ውስጥም ቢሆን እንኳ (ኢየሱስ የነበሩት ቅዱሳት መጻሕፍት እነዚህ ብቻ ነበሩ) ስለ ኢየሱስ የተነገረውን መፈለግ አለብን:: ኢየሱስ ሁሉንም አሟልቷል:: «በሙሴ ሕግ፣ በነቢያትና በመዝሙር መጻሕፍት» የሚለው የዕብራውያንን መጽሐፍ ቅዱስ ሦስት ዋና ዋና ምድቦች ይወክላል:: በዚህ ዘመን አነጋገር ሉቃስ፣ «ኢየሱስ መጽሐፍ ቅዱስን ከዳር እስከ ዳር አብራራላቸው» እንደ ማለት ነው:: እንዲህ ሲባል ግን እያንዳንዱ ጥቅስ ወደ ኢየሱስ ያመለክታል ማለት አይደለም:: ይልቁንም እያንዳንዱ መጽሐፍ ለኢየሱስ ያዘጋጃል፤ ስለ ኢየሱስ ትንቢት ይናገራል ማለት ነው::



ሁለተኛ፣ ሉቃስ 24÷45 ኢየሱስ መጽሐፍ ቅዱስን ማስተዋል እንድንችል እንደሚረዳን ያስተምራል:: በአሁኑ ጊዜ ያን ሥራ መንፈስ ቅዱስ ወስዶታል (ዮሐ 16÷13-15፤ 1ቆሮ 2÷10-16):: ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ አዲስ ዓይነት መገለጥ ይሰጠናል ማለት አይደለም:: የእርሱ ሥራ መጽሐፍ ቅዱስን ከማብራራት በላይ ቅዱሳት መጻሕፍትን በሕይወታችን ተግባራዊ ማድረግ የምንችልበትን መንገድ ማሳየት ነው:: የእግዚአብሔርን ልብ በመስጠት መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት እንድንችል ይረዳናል:: እግዚአብሔር ቅድሚያ ለሚሰጠው ቅደሚያ ስንሰጥ፣ ዓላማውን ስንጋራና ጸጋውን ስናደንቅ ቃሉ ይከፈትልናል:: መጽሐፍ ቅዱስን የሚያውቁ ለክርስቶስ ግን ያልተሰጡ በሚገባ የተማሩ ሰዎች አሉ:: ፍቺው ምን ማለት እንደ ሆነ ግን አያውቁም:: «መንፈሳዊ ያልሆነ ሰው ከእግዚአብሔር መንፈስ የሆነውን ነገር ለመቀበል አይችልም፤ ምክንያቱም እንዲህ ያለው ነገር ለእርሱ ሞኝነት ነው፤ በመንፈስም የሚመረመር ስለ ሆነ ሊረዳው አይችልም» (1ቆሮ 2÷14)::

ሦስተኛ፣ ትርጓሜ ወንጌልን በማዳረስ ላይ ማትኰር አለበት:: ከኀጢአታችን የሚያነጻንና ለጽድቅ የሚያስነሣንን የኢየሱስን ሞትና ትንሣኤ ማዕከል ማድረግ አለበት:: የተማርነውንም በጉጉት ለሚጠብቁን ዓለም ማድረስ አለብን:: በእግዚአብሔር መንግሥት ለግል ብቻ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት የሚባል ነገር የለም:: እግዚአብሔር በራሱ ላይ በሚያጠነጥን፣ ጥያቄና መልስ በሚያበዛ፣ አስተሳሰብን በሚቀርጽ ሆኖም ለሌላው በማይተርፍ ሃይማኖታዊ ምርምር እምብዛም አይጠቀምም:: እግዚአብሔር አማኞች እርስ በርስ የሚከራከሩበት ሆኖም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ወደ መፈጸም የማያደርስ አስተምህሮ ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እግዚአብሔርን አያስከብርም:: እንደ ሌሎች ወንጌላውያን ሁሉ ሉቃስ ለመላው ዓለም ወንጌልን ስለ ማዳረስ ጉዳይ አጽንዖት ይሰጣል::

ሉቃ 24፥49
ሐ/ሥ 1፥4 ጋር

49እኔም አባቴ የሰጠውን ተስፋ እልክላችኋለሁ፤
እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም
ከተማ ቆዩ:: (እኔ ስናገር የሰማችሁትን፣ አብ
የሰጠውን ተስፋ ጠብቁ[ሐ/ሥ])::

ሐ/ሥ 1፥5-8

5ዮሐንስ በውሃ አጥምቆ ነበርና፣ እናንተ ግን
ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ::
6እነርሱም፣ ተሰብስበው ሳሉ፣ «ጌታ ሆይ፤ የእስራኤልን መንግሥት መልሰህ
የምታቋቁምበት ጊዜው አሁን ነውን? ብለው ጠየቁት:: 7እርሱም እንዲህ አላቸው፤
«አብ በገዛ ሥልጣኑ የወሰነውን ጊዜ ወይም ወቅት ማወቁ ለእናንተ
አልተሰጣችሁም፤ 8ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በሚወርድበት ጊዜ ኃይልን
ትቀበላላችሁ፤ በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳና በሰማርያ ሁሉ፣ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ
ምስክሮቼ ትሆናላችሁ::

ደቀ መዛሙርት የኢየሱስ መሪነት፣ ወዳጅነትና ትምህርት ያስፈልጋቸው ነበር:: እርሱ ግን ወደ አብ መመለስ ነበረበት:: ስለዚህ ኀላፊነቱን ለመንፈስ ቅዱስ ሰጠ:: ታላቁን ተልእኮ በመፈጸም ረገድ በአካል ከተገደበው ኢየሱስ ይበልጥ ፍሬያማ ይሆናል::

ሐዋርያት በዓለ ሃምሳን ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ:: ወደ ገሊላ ከመመለስ ይልቅ ቢያንስ በመንፈስ ቅዱስ እስኪጠመቁ ድረስ በኢየሩሳሌም እንዲቆዩ መመሪያ ተሰጥቷቸዋል:: ይህ ደግሞ ሩቅ አይሆንም ፣አሥር ቀን በኋላ መንፈስ ቅዱስ በአካል በእነርሱ ላይ መጣ (ሐ/ሥ 2፥1-4) በግልጽ ኀይሉን ገለጠ:: ጴጥሮስ የቤተ ክርስቲያን በሮች ለመክፈት በነበረው ቁልፍ ተጠቀመ፤ 3000 ሰዎች ገቡ፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ተወለደች:: ስለሆነም ዓለም አቀፋዊ ዘመቻ ተጀመረ::[34]

[34] ይህን ምንባብ አስመልክቶ በሐዋርያት ሥራ ብዙ ሐሳብ ሊሰጥባቸው የሚገባ ነገሮች አሉ:: ይሁን እንጂ፣ ከጊዜ አንጻር ነገሩን በሐዋርያት ሥራ ላይ ለተጻፉ ሌሎች መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያዎች እንተዋለን::



§ 184
ዕርገቱ
([ማር 16፥19-20]፤
ሉቃ 24፥50-53፤
ሐ/ሥ 1፥9-12)

ይህ አስገራሚ ሁኔታ የኢየሱስን ክብርና ከፍ ማለት ሙሉ አደረገው:: ከሞት መነሣት ብቻ ሳይሆን ወደ አብ ቀኝ ከፍ ከፍ አለ:: ሥራውን ለመፈጸም ተቀምጧል፤ ማንኛውም ዳኛ የሚያደርገው ይህን ነው (ዕብ 1፥3፤ 12፥2):: ዳኛ ብቻ ሳይሆን የሚሟገትልን ጠበቃም ነው (ሮሜ 8፥34) ወይም ደግሞ የዕብራውያን መልእክት እንደሚለው የሚማልድልን ሊቀ ካህናት ነው (4፥14፤ 8፥1፤ 9፥11፤ 10፥12):: እግዚአብሔር እጅግ ከፍ ከፍ አደረገው (ፊልጵ 2፥9-11)፣ በሰማያት ላይ ሥልጣን ሰጠው (ኤፌ 1፥20-23):: ይበልጥ አስገራሚው ግን ገና አልመጣም:: ኢየሱስ እንዳረገ ሁሉ እኛም እናርጋለን (ቈላ 3፥1)! ትንሣኤውን እንደምንካፈል ሁሉ፣ ክብሩንም እንካፈላለን:: የወንጌል መደምደሚያም ይኸው ነው::

ሉቃ 24፥50-51
ማር 16፥19፤
ሐ/ሥ 1፥9 ጋር

50ከዚህ በኋላ እስከ ቢታንያ ይዞአቸው ወጣ፤
(ጌታ ኢየሱስ ይህን ከተናገራቸው በኋላ[ማር]) እጆቹን አንሥቶ
ባረካቸው:: 51እየባረካቸውም ሳለ፣ ከእነርሱ ተለይቶ
(እያዩት[ሐ/ሥ]) ወደ ሰማይ ዐረገ:: (ደመናም ከዐይናቸው
ሰወረችው[ሐ/ሥ]) (በእግዚአብሔርም ቀኝ ተቀመጠ[ማር])::

ሐ/ሥ 1፥10-12
ሉቃ 24፥52 ጋር

10እርሱም በሚሄድበት ጊዜ ትኩር ብለው ወደ
ሰማይ ሲመለከቱ፣ እነሆ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች
ድንገት አጠገባቸው ቆሙ፤ 11እንዲህም አሏቸው፤ «እናንተ

ሆኖም፣ ይህን ልብ ማድረግ ይኖርብናል፤ የሐዋርያት ሥራ የወንጌል ታሪክ ቀጣይ ነው:: 1፥1፣ «ቴዎፍሎስ ሆይ፤ ኢየሱስ ለማድረግና ለማስተማር የጀመረውን ሁሉ ቀደም ባለው መጽሐፌ ጽፌልሃለሁ» ይላል:: የሐዋርያት ሥራ በዮሐንስ ወንጌል መጀመሪያ በሥጋ በነበረ ጊዜ ኢየሱስ ስለ ሠራው ሥራ ይናገራል:: በሁለተኛው መጽሐፍ በረዳቱ በመንፈስ ቅዱስ በኩል ኢየሱስ በማከናወን ላይ ስላለው ተግባር ይናገራል:: ያለ ሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የአራቱ ወንጌሎች መልእክት የተሟላ አይሆንም ነበር::

የገሊላ ሰዎች ሆይ፤ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ እዚህ የቆማችሁት ለምንድነው? ይህ ከእናንተ ዘንድ ወደ ሰማይ ሲያርግ ያያችሁት ኢየሱስ፣ ልክ ወደ ሰማይ ሲወጣ እንዳያችሁት በዚሁ ሁኔታ ይመለሳል::

[12]ከዚያም (ሰገዱለት[ሉቃ]) ደብረ ዘይት ከተባለው ተራራ (በታላቅ ደስታ[ሉቃ]) ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፤ ይህም ተራራ ከኢየሩሳሌም የሰንበት መንገድ ያህል ይርቅ ነበር::

[53]እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ ዘወትር በቤት መቅደስ ነበሩ:: **ሉቃ 24÷53**

ከበዓለ ሃምሳ አስር ቀን በፊት ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እየመራ ወደ [*pros*] ቢታንያ ወሰዳቸው (ሉቃ 24÷50):: ስድስት ሳምንት ቀደም (ሐሥ 1÷12)[35] ሲል የድል ጉዞ በተጀመረበት ደብረ ዘይት በሚባለው ተራራ አናት ላይ ቆሙ:: በዚያ ለመጨረሻ ጊዜ ለሐዋርያቱ ተናገረ:: ምናልባትም በዚህ ወቅት መቶ ሃያዎቹም እዚያ ሳይገኙ አልቀሩም (ሐሥ 1÷15):: እጆቹን አንሥቶ ባረካቸው::[36] ምድራዊ አገልግሎቱ በዚህ ሁኔታ አበቃ:: ሲባርካቸው ሳለ፤ ከእነርሱ ተለይቶ መንሳፈፍ ጀመረ:: በሥጋ በነበረ ጊዜ ውሃ ላይ መራመድ ይችል እንደ ነበር ያውቃሉ:: ከሞት የተነሣ አካሉ በተዘጋ በር ለማለፍ እንደሚችልም ያውቃሉ:: ይህ ግን በጣም ገርሟቸዋል:: ፊኛ ወደ ሰማይ የወጣባቸው ሕፃናት ይመስል ትኩር ብለው ወደ ሰማይ ይመለከቱ ነበር:: በመጨረሻ ሙሉ በሙሉ ከዐይናቸው ተሰወረ፤ እነርሱ ግን አሁንም ትኩር ብለው ወደ ሰማይ ይመለከቱ ነበር:: ነጭ

[35] Cf. P. Atkins, "Luke's Ascension Location - A Note on Luke 24:50," *ExpT* 109/7 (1998): 205-206.

[36] ላይፌልድ (ገጽ 1058) ላይ ሉቃስ «ባረካቸው» [*eulogeo*] የሚለውን ቃል የተጠቀመው መጽሐፉ መጀመሪያና መጨረሻ ላይ መሆኑን አስተውሏል (1÷22:42:64፤ 2÷28:34፤ 24÷30:51:53):: ስለዚህም ሉቃስ ቃሉን የተጠቀመበት የመጀመሪያውን መጽሐፍ በተመሰከተ «ታሪኩ እያበቃ ነው» የሚል መልእክት ለማስተላለፍ በማሰብ ይሆናል::



ልብስ ለብሰው ጐናቸው የቆሙትን ሁለት መላእክት ያስተዋላቸው አልነበረም::

የገሊላዎቹ ደቀ መዛሙርት እስኪያውቋቸው ድረስ መላእክቱ እዚያ ለምን ያህል ጊዜ እንደ ቆዩ አናውቅም:: በመጨረሻ፣ «እናንተ ሰዎች፣ እንዲህ ትኩር ብላችሁ ወደ ሰማይ በማንጋጠጥ እስከ መቼ ልትቆዩ ነው?» የሚል ጥያቄ በማቅረብ ዝምታውን ሰበሩ:: ቀጥለው፣ «ይመለሳል!» አሏቸው፤ አንድምታው ግልጽ ነው፤ ወደ ሥራ ሂዱ! ከመመለሱ በፊት መሠራት ያለበት ሥራ አለ:: እንደሚጠበቀው ለኢየሱስ ሰገዱ፤ ቀጥሎ እግዚአብሔር የሚያደርገውን ለመጠበቅ በታላቅ ደስታ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ::

ዕርገቱ አስገራሚና ተአምራዊ ነገር መሆኑ ግልጽ ነው:: ይህን የጻፈው ግን ሉቃስ ብቻ ነው:: ምናልባት አንዳንዶች የሆነውን ተጠራጥረው ይሆናል:: ይሁን እንጂ የዕርገቱን ታሪካዊ እውነት አስመልክቶ ስቶት የተባለው ጸሐፊ አሳማኝ መከራከሪያዎችን አቅርቧል::

1. አስቀድሞ ተነግሯል (መዝ 110÷1፤ ሉቃ 22÷69)::
2. በአዲስ ኪዳን ታውጇል (ማር 16÷19፤ ሉቃ 24÷50-51፤ ሐሥ 1÷9-11)::
3. አዲስ ኪዳን ተቀብሎታል (ዮሐ 20÷17፤ ሐሥ 7÷55፤ ሮሜ 8÷34፤ 1ቆሮ 15÷1-28፤ ኤፌ 1÷18-23፤ ፊልጵ 2÷9-11፤ 3÷10:20፤ ቈላ 3÷1፤ ዕብ 1÷3፤ 4÷14፤ 8÷1፤ 9÷11፤ 10÷12፤ 12÷2፤ 1ጴጥ 3÷21-22)::
4. እንደ ራእይ መጻሕፍት ሳይሆን፣ ሁሉም በውናቸው ያዩት ጉዳይ ነው::
5. ምስክሮች ነበሩ::

6. ከትንሣኤው በኋላ መታየት[37] ጀምሮ ድንገት ስላቋረጠበት ምክንያት ሌላ ገለጻ መስጠት አይቻልም::

ስለሆነም ዕርገቱ ታሪካዊ እውነት መሆኑን እንቀበላለን:: ይህ ምን ማለት ነው? በመጀመሪያ፣ የኢየሱስ ሥራ አብቅቷል (ዮሐ 17÷4-5፤ 19÷30፤ ፊልጵ 2÷6:9-10):: የመጣበትን አጠናቋል፤ አሁን የሚሄድበት ጊዜ ደርሷል:: ሁለተኛ፣ በእግዚአብሔር ቀን ስለ ቅዱሳን የሚማልድበትን አዲስ ሥራ የሚጀምርበት ጊዜ መጥቷል (ሮሜ 8÷34፤ ዕብ 7÷25):: እንደሚሄድና ስፍራ እንደሚያዘጋጅ ቃል ገብቷል (ዮሐ 14÷2):: በመጨረሻ ምናልባትም በጣም አስፈላጊው፣ መንፈስ ቅዱስ የሚመጣው ኢየሱስ ካረገ በኋላ ነው (ዮሐ 7÷39፤ 16÷7):: ኢየሱስ ሥራውን ለመሥራት የሚችል እራሱ ብቻ ነበር:: አሁን ግን ኀላፊነቱን ለመንፈስ ቅዱስ የሚስተላልፍበት ጊዜ መጥቷል:: እንደሚመለስ ተስፋ የተሰጠው በዕርገቱ ነው፤ አሁን ጌታ በአካል ከእኛ ጋር ባይኖር እንኳ ለዘላለም በፊቱ ለመሆን የሚስችለንን ኀይል የምናገኘው በእርገቱ ነው::

[20]ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ ወጥተው፣ በየስፍራው ሁሉ ሰበኩ፤ ጌታም ከእነርሱ ጋር ይሠራ ነበር፤ ትምህርታቸውንም ተከትለው በሚፈጸሙ ምልክቶች ቃሉን ያጸና ነበር::

**ማር 16÷20**

ይህን በመሰለ ሁኔታ የኢየሱስ ታሪክ ሲያበቃ፣ የሙሽራይቱ ታሪክ ጀመረ:: በክብር በደመና እስኪገለጥ ድረስ የእርሱ ኀይል ስብከታችንን ይሙላው:: ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ ና::

[37] J. Stott, *The Spirit, the Chruch and the World* (Downers Grove: IVP, (1990): pp. 47-49.